

S/N/N/P/R/G/GURAGE ZONE GETTA WOREDA REVENUE AUTHORIT

ቁጥር:- ጌ/ወ/ገ/------/2014

ቀን:- ----/---/2014 ዓ.ም

ለጉራጌ ዞን ገቢዎች *መምሪያ*

<u>ወ ል ቂ ጤ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የማዘጋጃ ቤቶች ሞዴል መመሪያ 49/2014 መሰረት የተጠናዉ ጥናት</u>

<u>መረጃ አስተያየት እንዲሰጥነት ስለመላክ</u>

ከላይ በርዕሱ ለመግለጽ እንደተሞከረው የጌታ ወረዳ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት የማዘጋጃ ቤቶች ሞዴል መመሪያ 49/2014 መሰረት የተጠናዉ ጥናት መረጃ የሶስቱም ማዘጋጃዎች የትናት መረጃ አስተያየት እንዲሰጥነት ከዚህ ሸኝ ደብዳቤ ጋር በ----ገጽ አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን።

“ግብር ለሀገር ክብር”

<u>ግልባጭ</u>

- **ለጽ/ቤታችን ኃላፊ**
- **ለጌታ ወረዳ ዋና አስተዳደር**
- **ከ/ል/ኮ ጽ/ቤት**
- **ለቋንጤ ከተማ ማዘጋጃ ቤት**
- **ለቀቡል ታዳጊ ማዘጋጃ ቤት**
- **ለእስኩት ታዳጊ ማዘጋጃ ቤት**

<u>ቋ ን ጤ</u>

መመሪያ **05/2014** **ዓ.ም**

የደቡብ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በጉራጌ ዞን የጌታ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት

ከተማ መሬት እና ቤት ጋር ተያያዥነት ያላቸው የአገልግሎት ክፍያ ማዕቀፍ ለመወሰን የወጣ *መመሪያ*

<u>መግቢያ</u>

የከተማ *መሬት* በየትኛውም የአለም ክፍል ትልቅ የኢኮኖሚ ምንጭ በመሆኑ *መሬት*ን በአግባቡ በመያዝና ጥቅም ላይ ማዋል ለከተሞች ዕድገት እጅግ አስፈላጊና ወሳኝ ናቸው።

በአንድ ከተማ ውስጥ የሚገኝ የከተማ *መሬት* እና ቤት ከተማው ለነዋሪው ህብረተሰብ ሊያቀርብ የሚገባውን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎት *መስ*ጫ ተቋማት እና *መሠረተ* ልማቶችን ለማሟላት አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው የገቢ ምንጭ በመሆናቸው ከዘርፉ የሚመነጨውን ገቢ አሟጦ በመሰብሰብ ለከተማው ዕድገት እና ለነዋሪ ህብረተሰብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፍላጎት ለማሟላት አስፈላጊ በመሆኑ፣

ከከተማ *መሬት* እና ቤት ጋር ተያያዥነት ያላቸው የአገልግሎት ክፍያ ተመን ግልፅነትና ተጠያቂነት የሰፈነበት፣ ወጥነት ያለውና ወቅታዊ የሆነ እንዲሁም ከሚሰጠው አገልግሎት ጋር ተመጣጣኝ የአገልግሎት ክፍያዎች *መ*ጣኔ ተመን በመለየት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ለማስተናገድ እንዲሁም *መ*ክፈል የሚገባቸው ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ *መ*ክፈል እንዲችሉ መወሰን በማስፈለጉ፣በሥራ ላይ ያለው የ*መ*ጣኔ ማዕቀፍ ለአምስት አመታት ያህል የቆየ በመሆኑ አገልግሎቱን ለማቅረብ የሚወጣው ወጪ ከወቅቱ የኢኮኖሚ ተለዋዋጭነት እና የገበያ ሁኔታ ጋር ለማጣጣም እና ማዘጋጀ ቤታዊ አገልግሎቶችን ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ቀላል፣ ምቹ፣ ጊዜ ቆጣቢና ፍትሃዊ እንዲሆን የአገልግሎት ክፍያ ማዕቀፍ ማውጣት እና ለአገልግሎት *መስ*ጫ የሚከፈለውን የ*መ*ጣኔ ተመን መወሰን በማስፈለጉ፤

በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል *መ*ንግሥት የከተሞች የንብረት ግብር እና አገልግሎት ክፍያ ደንብ ቁጥር 83/2003 አንቀጽ 13 **መሠረት ከተሞች የገቢ ርዕሰ*ቻ*ቸውን እና የ*መ*ጣኔ ተመን ከራሳቸው አካባቢያዊ ሁኔታ አንፃር እንዲያዘጋጁ በተደነገገው *መ*ሠረት <u>**የጌታ ወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት**</u> ይህንን *መመሪያ* አውጥቷል።**

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

፩.አጭር ርዕስ

ይህ *መመሪያ* "ከከተማ *መሬት* እና ቤት *ጋር* ተያያዥነት ያላቸው የአገልግሎት ክፍያዎች ማዕቀፍ ለመወሰን የወጣ *መመሪያ* ቁጥር 05/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪.ትርጓሜ

ለቃሉ ወይም ለሐረጉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለዚህ *መመሪያ* አፈፃፀም ሲባል፤

፩. "ክልል" ማለት የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ነው።

፪. "ጽ/ቤት" ማለት የገቢዎች ጽ/ቤት ነው።

፫. "ቢሮ" ማለት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ነው።

፭. "የወረዳ ምክር ቤት" በህዝብ ምርጫ የሚቋቋም ህግ አውጪ የመንግስት ሥልጣን አካል ነው።

፮. “የከተማ ፕላን ወሰን” ማለት ለአንድ ከተማ በከተማ ፕላን መሠረት ለተወሰነ የፕላን ዘመን

በካርታ የተካለለ የከተማው የመሬት አጠቃቀም ወሰን ነው።

፱. "ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት" ማለት የከተሞችን ነዋሪ ሕብረተሰብ ፍላጎት ከማርካትና

ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ከመቅረፍ አንፃር በሁሉም ከተሞች የሚሰጥ የከተማ ነክ

አገልግሎት ነው፣

፲."ፊርጅ" ማለት ከተሞች በፖለቲካዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በማህበራዊ ልማት እንቅሰቃሴ ሂደት

የደረሱበትን የዕድገት ደረጃ ለመመዘን ከተዘጋጁት መስፈርቶች አንጻር ባመጡት ድምር ውጤት መሠረት የተሰጣቸው የከተማነት ደረጃ ነው፣

፲፩. "የመጣኔ ተመን" ማለት ከማንኛውም ሰው የሚፈለግበትን ግብር እና የአገልግሎት ክፍያዎች መጠን ለማስላት የሚያገለግል እንደገቢው ዓርዕስት ዓይነት፣መስፈርትና መለኪያ የሚለያይ ሆኖ በከተማው የልማት ፍላጎት እና በህብረተሰቡ የመክፈል አቅም መሰረት የሚተመን ነጠላ የማስከፈያ ተመን ነው።

፲፪. “ሕንፃ ወይም ቤት” ማለት ለመኖሪያ፣ ለቢሮ፣ ለፋብሪካ ወይም ለማናቸውም ሌላ አገልግሎት የሚውል ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ግንባታ ነው። ሆኖም ክዳኑ ሳር፣ ግድግዳው እንጨትና ጭቃ የሆነን ቤት አይጨምርም።

፲፫. “ግንባታ” ማለት አዲስ ሕንፃ መገንባት ወይም ነባር ሕንፃን ማሻሻል ወይም አገልግሎቱን

መለወጥ ነው።

፲፬. “የግል መኖሪያ ሕንፃ” ማለት ለአንድ ቤተሰብ መኖሪያነት የሚያገለግሉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ክፍሎች ያሉት ሆኖ የመፀዳጃና የማብሰያ አገልግሎቶች የሚሰጡ በመኖሪያው ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኙ መኪና ማቆሚያና ለመኖሪያነት የሚውሉ ከዋናው ቤት የተነጠሉ ክፍሎችን ሊጨምርይችላል።

፲፭. “ፎቅ” ማለት በሁለት ወለሎች መካከል ወይም ከላይ ሌላ ወለል የሌለ በወለሉና በኰርኒስመሃል ያለው የሕንፃ ክፍል ነው።

፲፮. “የግንባታ ዲዛይን ወይም ፕላን” ማለት የአንድን ሕንፃ መጠን፣ ዓይነትና ስፋት እንዲሁም ሕንፃው የሚሠራበትን ቁሳቁስና የአገነባብ ዘዴን የሚያሳይ ንድፍ ወይም ሞዴል ሲሆን የአርክቴክቸር፣ የስትራክቸር፣ የሳኒተሪ፣ የኤሌክትሪካል፣ የሜካኒካል፣ የእሳት መከላከልና የሌሎች ሥራዎችን ንድፍ ሊያካትት ይችላል።

፲፯. “የፕላን ስምምነት” ማለት ስልጣን ባለው አካል ለህንፃ ግንባታ የቀረበ የግንባታ ዲዛይን ወይም ፕላን ከከተማው ፕላን ጋር መጣጣሙን ለማረጋገጥ የሚሰጥ የጽሁፍ ስምምነት ነው::

፲፰. “ምድብ ‘ሀ’ ሕንፃ” ማለት በሁለት የኮንክሪት ወይም የብረት ወይም ሌሎች ስትራክቸራል ውቅሮች መካከል ያለው ርቀት 7 ሜትር ወይም ከዚያ በታች የሆነ ባለአንድ ፎቅ ሕንፃ ወይም ማናቸውም ከሁለት ፎቅ በታች የሆነ የግል መኖሪያ ቤት ነው።

፲፱. “ምድብ ‘ለ’ ሕንፃ” ማለት በሁለት የኮንክሪት ወይም የብረት ወይም ሌሎች ስትራክቸራል ውቅሮች መካከል ያለው ርቀት ከ 7 ሜትር በላይ የሆነ ወይም ባለሁለት ፎቅና ከሁለት ፎቅ በላይ የሆነና በምድብ ‘ሐ’ የማይሸፈን ሕንፃ ወይም በምድብ ‘ሀ’ የተመደበ እንደሪል ስቴት ያለ የቤቶች ልማት ነው።

፳. “ምድብ ‘ሐ’ ሕንፃ” ማለት የሕዝብ መገልገያ ወይም ተቋም ነክ ሕንፃ፣ የፋብሪካ ወይም የወርክ ሾፕ ሕንፃ ወይም ከመሬት እስከ መጨረሻው ወለል ከፍታው ከ 12 ሜትር በላይ የሆነ ማናቸውም ሕንፃ ነው።

፳፩. “የከተማ ቤት ግብር” ማለት ከተማው በሕግ እንዲያስተዳደር በተፈቀደለት መሬት ላይ ከተገነባ ቤት የሚሰበሰብ ክፍያ ነው።

፳፪. “የሕንፃ ግንባታ ዋጋ ግምት” ማለት የቤቱ ወይም ሕንፃው ግንባታ ፍቃድ በተሰጠው ፕላን መሠረት የሚዘጋጅ የቤት ወይም ሕንፃ ዋጋ ግምት ወይም ፕላን የሌለው ከሆነ የማዘጋጃ ቤቱ መሐንዲስ የሚያዘጋጀው የግንባታ ወጪ ነው። ይህ ግምት የመሬትና የአካባቢ ዕድገት ዋጋን አያካትትም።

፳፫. “ሊዝ” ማለት የከተማ ቦታ የመጠቀም መብት በጊዜ በተገደበ ውል የሚተላለፍበት ወይም የሚያዝበት የመሬት ስሪት ዓይነት ነው።

፳፬. “የሊዝ መነሻ ዋጋ” ማለት ዋና ዋና የመሰረተ ልማት አውታሮች የመዘርጊያ ወጪን፣ ነባር ግንባታዎች ባሉበት አካባቢ የሚነሱ ግንባታዎች እና ንብረቶችን ለማንሳት የሚያስፈልገውን ወጪን እና ለተነሺዎች የሚከፈል ካሳን እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው መስፈርቶችን ታሳቢ ያደረገ የመሬት የሊዝ ዋጋ ነው፤

፳፭. **“የሊዝ መብት ማስተላለፊያ ዋጋ”**ማለት ግንባታ ያልተከናወነበት ወይም ግማሽ እና ከግማሽ በታች የተገነባ ግንባታ ያረፈበትን የሊዝ መሬት የመጠቀም መብት በሕጉ መሰረት ሲተላለፍ በተገቢው አካል የአካባቢውን የሊዝ መሬት ጨረታ ዋጋ መሰረት በማድረግ የሚወሰን ዋጋ ነው። የሊዝ መብቱ በሻጭ የተገዛበት ሲደመር ግብይቱ በሚከናወንበት ወቅት ያለው የአካባቢ ከፍተኛ የጨረታ ዋጋ ድምር ለሁለት ተካፍሎ የሚገኝ የሂሳብ ውጤት ወይም በተገቢው አካል በደንቡ በተቀመጠው መሰረት ስምምነት የሰጠበት ዋጋ ነው።

፳፮. **“ነባር ይዞታ”** ማለት ከተማው በሊዝ ስርዓት መተዳደር ከመጀመሩ በፊት በሕጋዊ መንገድ የተያዘ ወይም ሊዝ ተግባራዊ ከሆነ በኋላ ለነባር ይዞታ ተነሺ በምትክ የተሰጠ ወይም ሊዝ ከመተግበሩ በፊት የተያዘ ሆኖ አግባብ ባለው አካል ከሊዝ ስሪት ውጭ እንዲቀጥል በህግ እውቅና የተሰጠው ቦታ ነው።ስም ተመዝግቦ የተያዘና የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት ነው።

፳፯. “አሹራ ማረጋገጫ መስጠት” ማለት ማዘጋጃ ቤቱ በአስተዳደሩ ስር የሚገኙትን ማንኛውንም

ሕንጻ ወይም ቤት ወይም ሌላ ቋሚ ንብረት ባለቤት ማን እንደሆነ ለጠያቂው ማረጋገጫ

መስጠት ነው።

፳፱. “የውጭ ማስታወቂያ” ማለት፣

ሀ) በቢልቦርድ፣ በኤሌክትሮኒክ ስክሪን ወይም በተንቀሳቃሽ ምስል የሚሰራጭ፤

ለ) በሕንጻ ወይም በማናቸውም ስትራክቸር ወይም በትራንስፖርት ተሽከርካሪ ላይ የሚዋፍ ወይም የሚለጠፍ፤

ሐ) በተንጠልጣይ ነገር፣ በፖስተር፣ በስቲከር፣ በብሮሸር፣ ሊፍሌት ወይም በራሪ ወረቀት የሚሰራጭ፤

መ) በድምጽ ካሴት፣ በድምፅ ማጉያ መሳሪያ የሚሰራጭ፤ ወይም

ሠ) በሌላ መሰል ማሰራጫ መንገድ አማካኝነት የሚሰራጭ፤

ማስታወቂያ ነው።

፴. “ቅጣት” ማለት በዚህ መመሪያ የተገለጹትን ድንጋጌዎች የጣሰ ግለሰብም ሆነ ተቋም

የሚከፍለው አስተዳደራዊ ቅጣት ነው።

፴፩. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

፫.**የፆታ አገላለጽ በ**ዚህ መመሪያ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴት ጾታንም ይጨምራል።

፬. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በጌታ ወረዳ ውስጥ በሚገኙ ማዘጋጃ ቤቶች የአገልግሎት ተጠቃሚዎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

፭. ከከተማ መሬት እና ቤት ጋር በተያያዘ ገቢ የሚሰበሰብባቸው ዋና ዋና የገቢ አይነቶች

፩. የከተማ ቤት ግብር፣

፪. የከተማ ቦታ ኪራይና ሊዝ፣

፫. የመደብ ኪራይ፣

፬. የበረት አገልግሎት፣

፭. የቤትና አጥር የግንባታ ፈቃድ የመስጠት አገልግሎት፣

፮. የምህንድስና አገልግሎት፣ የሕንፃ ምድብን መሠረት ያደረገ የሕንፃ ቁጥጥር አገልግሎት፣

፯. የዲዛይን ጥናት፣ የዋጋና የጨረታ ሰነድ ዝግጅት እና ፕላን የመገምገም አገልግሎት፣

፰. የመሬት ባለይዞታነት እና የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እና ምትክ ማስረጃ የመስጠት

አገልግሎት፣

፱. የባለይዞታነት እና የቤት ባለቤትነት የስም ዝውውር የውል ምዝገባ አገልግሎት፣የይዞታ ሰነድ ህጋዊነት የማረጋገጥና ማስረጃ የመስጠት አገልግሎት፣

፲. የእዳና እገዳ ምዝገባና ስረዛ የመስጠት አገልግሎት፣

፲፩. የውጭ ማስተዋወቅ ፈቃድ የመስጠት አገልግሎት ናቸው።

ክፍል ሁለት

ለአገልግሎቶች የሚፈጸም ክፍያዎች

፯. የአገልግሎት ክፍያዎች መጣኔ ተመን አወሳሰን መርህ

፩. የአገልግሎት ክፍያ አወሳሰን ስርዓትን ለሁሉም አገልግሎት ተጠቃሚዎች ግልፅ የማድረግ፤ የከተማው ነዋሪ ህብረተሰብ ከከተማው ማዘጋጃ ቤት አገልግሎት የማግኘት መብት ያለው መሆኑን የማሳየት እንዲሁም የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ለሚያገኘው አገልግሎት ተመጣጣኝ ዋጋ የማስከፈል።

፪. በአነስተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ቢያንስ መሰረታዊ የሆኑ አገልግሎቶችን

በነፃ እንዲያገኙ የማስቻል።

፫.የአገልግሎት ክፍያዎች ተመን ሲወሰን አገልግሎቱን ለመስጠት የሚወጣውን ወጪ፣የሚወስደውን ጊዜና መሰል ጉዳዮችን ሙሉ በሙሉ በአገልግሎት ክፍያ እንዲሸፈን ታሳቢ የማድረግ::

፬. የአገልግሎት ወጪን ለመተመን የተለዩ ወጪዎች አገልግሎቱን ለመስጠት የሚወጣውን ሙሉ ወጪ በወጪ መጋራት መንፈስ እንጂ የአገልግሎት ሰጭ አካል በበጀት የተመደበለትን የመደበኛ ወይም ሥራ ማስኬጃ ወጪ እንዳይሆን የማስቻል።

፭. የአገልግሎቱ ክፍያ የተተመነው ለአገልግሎቱ የገንዘብ ክፍያ በተፈጸመበት ጊዜ ሳይሆን በተወሰነ ጊዜ ገደብ ውስጥ ለአገልግሎቱ በሚያስፈልገው ወጪ ግምት ላይ የተመሰረተ መርህን የተከተለ ነው።

፮. የከተማ ቤት ግብር **(1701)** የመጣኔ ማዕቀፍ

፪. በሊዝ አዋጅ 721/2004 አንቀጽ (፯) ንዑስ አንቀጽ (፯) ለባለበጀት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና ለኃይማኖት ተቋማት በምደባ በሚሰጥ የከተማ ቦታ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም በሚለው ድንጋጌ የባለበጀት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና የኃይማኖት ተቋማት በሚኖራቸው ሕንፃ እና መሬት ላይ ግብር አይጠየቁም።

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኃይማኖት ተቋማት ከአምልኮ ውጪ ገቢ በሚያስገኝ የቤትና የመሬት ይዞታ መጠን ልክ ግብር ይከፍላሉ።

፱. በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ የኮንስትራክሽን ባለስልጣን በሚያዘጋጀው የቤት ወይም ሕንፃ የግንባታ ወጪ ትመና መመሪያ መሠረት በከተማው ማዘጋጃ ቤት ኮንስትራክሽን ዘርፍ የተመደበ ባለሙያ የእያንዳንዱን ቤት ግምት ለገቢዎች ቢሮ ያስተላልፋል።

፮.የገቢዎች ጽ/ቤት የደረሰውን ግምት መነሻ በማድረግ ለከተማ ቤት ግብር የሚከፈለውን የገንዘብ መጠን በማስላት በዚህ መመሪያ በተዘጋጀው ቅጽ መሠረት የክፍያ መጠን ለባለይዞታው እንዲደርስ ሊያደርግ ይችላል።

፯. በፈርጅ አራት እና አምስት የተመደቡ ከተሞች በኮንስትራክሽን ዘርፍ የመሀንዲስ የሥራ መደብ እስከሚያደራጁ ድረስ በቁርጥ የከተማ ቤት ግብር ይከፈላል። ዝርዝሩ በሰንጠረዥ አንድ ተመልክቷል።

፰. የከተማ ቦታ ኪራይ **(1721)** የነባር ይዞታ የመሬት ኪራይ መጣኔ ማዕቀፍ

፮. የከተማ ቦታ በሊዝ ስርዓት መተዳደር ከመጀመሩ በፊት በሕጋዊ መንገድ የተያዘ ቦታ ወይም

፪. ሊዝ ተግባሪዊ ከሆነ በኋላ ለነባር ይዞታ ተነሺ በምትክ የተሰጠ ቦታ የነባር የመሬት ኪራይ

ይከፈላል።

፫. በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ጽ/ቤት የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ኤጀንሲ እና የከተማ ፕላን ኢንስቲትዩት የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ የከተማ ቦታ ደረጃ ጥናት በማካሄድ

የቦታ ደረጃ ይለያሉ።

፬. የነባር የመሬት ይዞታ የመጣኔ ተመን በከተማ ፈርጅ፣ በዋናና ንዑስ የቦታ ደረጃዎች እንዲሁም

በአገልግሎት አይነትን በመለያየት ተዘጋጅቷል። ዝርዝሩ በሰንጠረዥ ሁለት ተመልክቷል።

ሠንጠረዥ አንድ፦ የከተማ ቤት ወይም ሕንፃ ግብር ለፈርጅ አራትና አምስት ከተሞች

ተ.ቁ	የአገልግሎት አይነት	መለኪያ	ፈርጅ አራት		ፈርጅ አምስት		የውሳኔ ሃሳብ	
1	የመኖሪያ ቤት ግብር		መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳብ(ለፈርጅ አራት)	የውሳኔ ሃሳብ(ለፈርጅ አምስት)
1.1	ከእንጨትና ከጭቃ የተሰራ ቤት	ብር	100	125	80	100	100	80
1.2	በድንጋይና ብሎኬት የተሰራ ቤት	ብር	275	300	200	250	300	200
1.3	ፎቅ ቤት (G+1- G+ 5)	ብር	450	500	400	450	450	400
1.4	ከ (G+5) ፎቅ በላይ	ብር	650	700	600	650	650	600
2	ከመኖሪያ ቤት ውጪ ግብር							
2.1	ከእንጨትና ከጭቃ የተሰራ ቤት	ብር	250	300	200	250	250	200
2.2	በድንጋይና ብሎኬት የተሰራ ቤት	ብር	450	500	400	450	450	400
2.3	ፎቅ ቤት (G+1- G+2)	ብር	650	700	600	650	650	600
2.4	ፎቅ ቤት (G+3- G+4)	ብር	800	900	750	850	850	800
2.5	ፎቅ ቤት (G+ 5- G+ 6)	ብር	1100	1200	1000	1100	1100	100
2.6	ከ (G+6) ፎቅ በላይ	ብር	1500	2000	1500	2000	1500	1500

ሠንጠረዠ ሁለት :-የነባር ይዞታ የከተማ መሬት ኪራይ ተመን የአንድ ካሬ ሜትር የዓመት ግብር በብር

ተ.ቁ	የከተማ ፊርጅ	የዋና ቦታ ደረጃ	የንዑስ ቦታ ደረጃ	የከተማ መሬት የአገልግሎት ዓይነት					
				ለንግድ	ለኢንዱስትሪ	ለማህበራዊ አገልግሎት	ለግል መኖሪያ	ለሚከራይ መኖሪያ ቤት	ለከተማ ግብርና
2.1	ፊርጅ አራት ከተማ	1ኛ	1	2.15	1.40	1.35	1.40	1.45	1.85
2.2			2	1.95	1.35	1.30	1.30	1.35	
2.3			3	1.90	1.30	1.25	1.25	1.25	
2.4		2ኛ	1	2.05	1.35	1.30	1.30	1.35	
2.5			2	1.85	1.30	1.25	1.25	1.30	
2.6			3	1.90	1.25	1.20	1.20	1.25	
2.7		3ኛ	1	2.00	1.30	1.25	1.25	1.30	
2.8			2	1.90	1.25	1.20	1.20	1.25	
2.9			3	1.85	1.20	1.15	1.15	1.20	
3	ፊርጅ	1ኛ	1ኛ	1.95	1.30	1.35	1.25	1.35	

ተ.ቁ	የከተማ ፈርጅ	የዋና ቦታ ደረጃ	የንዑስ ቦታ ደረጃ	የከተማ መሬት የአገልግሎት ዓይነት					
				ለንግድ	ለኢንዱስትሪ	ለማህበራዊ አገልግሎት	ለግል መኖሪያ	ለሚከራይ መኖሪያ ቤት	ለከተማ ግብርና
3.1	አምስት ከተማ		2ኛ	1.85	1.25	1.25	1.20	1.25	1.20
3.2		2ኛ	1ኛ	1.70	1.20	1.20	1.10	1.20	
3.3			2ኛ	1.45	1.10	1.05	1.05	1.15	

፱. የገበያ መደብ ኪራይ **(1725)** የመጣኔ ማዕቀፍ

፮. በገበያና በከተማ አካባቢ ለግብይት የሚያገለግል ቋሚ የገበያ መደብ ለመደብ ደረጃው የሚወሰነውን መጣኔ ተመን መነሻ በማድረግ በጨረታ ወይም በምደባ ለተጠቃሚ ይሰጣል። ውሉም በየዓመቱ ይታደሳል፡፡

፯. በቋሚነት ሳይሆን በጊዜያዊነት የገበያ እና የከተማ አካባቢ ቦታን ለግብይት አገልግሎት ከሚጠቀም ማንኛውም ሰው አገልግሎት በሰጠው ካሬ ሜትር ሲባዛ በሁለተኛ ደረጃ መደብ የተወሰነው የመጣኔ ተመን የሚገኘውን የገንዘብ መጠን ይከፍላል።

፲. የገበያ መደብ የመጣኔ ተመን ዋና የገበያ ማዕከል የመደብ ደረጃን እና ሌሎች ንዑስ የገበያ

ማዕከል የመደብ ደረጃን በመለየት ይዘጋጃል።

፲፩. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) የመደብ ኪራይ ዓመታዊ ክፍያ ውል ሲታደስ በዓመት አንድ ጊዜ አስቀድሞ ክፍያ የሚፈጸም ይሆናል። ሆኖም ግን በአንድ ጊዜ መክፈል የማይችል በየስድስት ወር እንዲከፍል ይደረጋል። ዝርዝሩ በሰንጠረዥ ሦስት ተመልክቷል።

ሰንጠረዥ ሦስት፡-የገበያ መደብ ወርሃዊ የኪራይ ተመን በካሬ ሜትር በብር

ተ ቁ	የገበያ መደብ ደረጃ	መለኪያ	ፈርጅ አራት		ፈርጅ አምስት			
			መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳብ(ለፈርጅ አራት)	የውሳኔ ሃሳብ(ለፈርጅ አምስት)
1	1ኛ ደረጃ መደብ	ብር	8	10	6	8	8	6
2	2ኛ ደረጃ መደብ	ብር	5	6	4	5	3	2
3	3ኛ ደረጃ መደብ	ብር	3	4	2	3	4	3
4	በመጀመሪያ መደቡን ሲረከቡ የገበያ መደብ ኪራይ መመዝገቢያ ለአንድ ጊዜ ብቻ በካሬ ሜትር	ብር	20	25	10	15	20	10
5	የገበያ መደብ ኪራይ ማደሻ በካሬ ሜትር በዓመት	ብር	10	12	8	10	10	8

፲. ከበረት ኪራይ **(1726)** የአገልግሎት ክፍያ የመጣኔ ማዕቀፍ

፩. በማዘጋጃ ቤት የሚተዳደር የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከል የበረት የአገልግሎት ክፍያይከፈላል።

፪. ለግብይት ከሚቀርብ እንስሳት በረቱን ለመገንባት፣ለመጠገንና ንጽህናውን ለመጠበቅ የሚወጣውን ወጪ ከግምት ውስጥ በማስገባት በእንስሳት አይነት በቀን ይከፈላል።

፫. የበረት ኪራይ የመጣኔ ተመን ዋና የበረት ገበያ እና ሌሎች ንዑስ የበረት ገበያ በመለየት ይዘጋጃል።

፬. ለግብይት የቀረቡ እንስሳት ተገዝተው በሚወጡበት ወቅት ገዢ ይከፍላል እንዲሁም ሳይሸጡ ለቀሩ እንስሳት የእንስሳቱ ባለቤት የበረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል።ዝርዝሩ በሰንጠረዥ አራት ተመልክቷል።

፭. በአዋጅ ቁጥር 819/2006 መሠረት ስለ ቁም እንስሳት ግብይት የሚቋቋሙ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት በአዋጁና ደንቡ መሠረት ተፈጻሚ የሚሆን ይሆናል።

ሰንጠረዥ አራት:-የበረት ኪራይ የአገልግሎት ክፍያ መጣኔ ማዕቀፍ

ተ ቁ	የእንስሳው አይነት	መለኪያ	ፈርጅ አራት		ፈርጅ አምስት			
			መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳብ(ለፈርጅ	የውሳኔ ሃሳብ(ለፈርጅ አምስት)

							አራት)	
1	ለቀንድ ከብት (በሬ፣ ላም ... ወዘተ) እና የጋማ ከብት (በቅሎ፣ ፈረስ፣ አህያ)፣ (ግመል)	በቀን/ ብር	25	60	20	50	25	25
2	ለበግ እና ለፍየል	በቀን/ ብር	10	20	10	20	15	15

፲፩.የመሰረተ ልማት ግንባታ የመብራት፣የውሃና የስልክ **(1729)** የሌሎች ኪራይ መጣኔ ማዕቀፍ

፩. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር የሚጣጣም አስገዳጅ

የከተማ መሬት መጠቀሚያ የአገልግሎት ክፍያ የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት በደንብ ይወሰናል።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ወደ መሬት ኪራይ የአገልግሎት ክፍያ ከመገባቱ በፊት የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር እና የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ከአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር በጋራ በመሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ ስምምነት ላይ በመድረስ ለከተሞች ለአፈፃጸም እንዲያርስ ይደረጋል።

፫. ለመብራትና ለስልክ ፖል ወይም ለውሃና ለስልክ መስመር እንዲሁም ለቴሌ ታወርና ለመብራት

ትራንስፎርመር የከተማ መሬት መጠቀሚያ የመጣኔ ማዕቀፍ በሰንጠረዥ አምስት ተመልክቷል፡

ሠንጠረዥ አምስት :-የመብራት፣ የውሃና የስልክ የአገልግሎት መጣኔ ማዕቀፍ

ተ.ቁ	የአገልግሎት አይነት	መለኪያ		ፈርጅ አራት		ፈርጅ አምስት			
				መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የወሳኔ ሃሳ ብ(ለፈርጅ አራት)	የወሳኔ ሃሳ ብ(ለፈርጅ አምስት)
1	የመሰረተ ልማት ማስፋፊያ፣ ማሻሻያና የጥገና ፍቃድ	በፍቃድ	ብር	250	500	250	500	350	300
2	የማስጀመሪያ ፈቃድ እና የክትትል አገልግሎት መስጠት	በፍቃድ	ብር	500	1,000	500	1,000	500	500
3	ለመብራትና ቴሌ ፖል መትከያ በምሰሶ	በቁጥር በአመት	ብር	3	4	3	4	4	4
4	በጉድጓድ ለሚቀበር ማስተር ኬብል	በሜትር በአመት	ብር	1	3	1	3	3	3
5	የመብራት ትራንስፎርመር	በካሬ ሜትር/ በቁጥር በአመት	ብር	10	15	10	15	10	10
6	ለቴሌ ታወር	በካሬ ሜትር	ብር	10	15	10	15	10	10
7	የውሃ መስመር አዲስ ሲገባ ለመኖሪያ	በሜትር	ብር	1	3	1	3	3	3
8	የውሃ መስመር አዲስ	በሜትር	ብ	1	3	1	3	3	3

ተ.ቁ	የአገልግሎት አይነት	መለኪያ		ፈርጅ አራት		ፈርጅ አምስት			
				መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የወሳኔ ሃሳብ (ለፈርጅ አራት)	የወሳኔ ሃሳብ (ለፈርጅ አምስት)
	ሲገባ ለድርጅት		ር						

ፓ፪. የመሬት ሊዝ **(1731)** መጣኔ ማዕቀፍ

፩. የከተማን ቦታ በሊዝ ስለመያዝ የወጣ አዋጅ 721/2004 አንቀጽ (14) ንዑስ አንቀጽ (3) የሊዝ መነሻ ዋጋ ወቅታዊነቱን ጠብቆ ቢያንስ በየሁለት ዓመቱ መከለስ እንዳለበት ተመልክቷል፤

፪. የመሬት ሊዝ መነሻ መጣኔ ተመን ሲዘጋጅ የመሬት የወቅቱን የቦታ ጨረታ ዋጋ አመላካች መስፈርት ሆኖ ተወስዷል።

፫. የከተማ መሬት ሊዝ መነሻ መጣኔ ተመን የከተማ ፈርጅ፣ የዋናና ንዑስ የቦታ ደረጃዎችን እና የአገልግሎቱን አይነት በመለያየት ተዘጋጅቷል። ዝርዝሩ በሰንጠረዥ ስድስት ተመልክቷል።

ሰንጠረዥ ስድስት:- የከተማ መሬት ሊዝ መነሻ ዋጋ የአንድ ካሬ ሜትር በብር እና በሊዝ ዘመን፣

ተ.ቁ	የከተማ ፈርጅ	የዋና ቦታ ደረጃ	የንዑስ ቦታ ደረጃ	የከተማ ቦታ የአገልግሎት ዓይነት					
				ለንግድ **(70)** ዓመት	ለኢንዱስትሪ **(80)** ዓመት	ለማህበራዊ አገልግሎት **(99)** ዓመት	ለግል መኖሪያ **(99)** ዓመት	ለሚከራይ መኖሪያ ቤት **(99)** ዓመት	ለከተማ ግብርና **(15)** ዓመት
	ፈርጅ አራት ከተማ	**1** ኛ	**1**	**273**	**170**	**225**	**100**	**115**	**86**
			2	**266**	**166**	**185**	**86**	**104**	
			3	**248**	**138**	**150**	**74**	**98**	

ተ.ቁ	የከተማ ፈርጅ	የዋና ቦታ ደረጃ	የንዑስ ቦታ ደረጃ	የከተማ ቦታ የአገልግሎት ዓይነት					
				ለንግድ (70) ዓመት	ለኢንዱስትሪ (80) ዓመት	ለማህበራዊ አገልግሎት (99) ዓመት	ለግል መኖሪያ (99) ዓመት	ለሚከራይ መኖሪያ ቤት (99) ዓመት	ለከተማ ግብርና (15) ዓመት
		2 ኛ	1	240	108	175	70	95	
			2	232	94	156	65	90	
			3	228	88	126	54	71	
		3 ኛ	1	221	80	117	50	61	
			2	200	76	100	46	56	
			3	190	70	80	43	50	
	ፈርጅ አምስት ከተማ	1 ኛ	1	228	88	126	54	71	75
			2	221	80	117	50	61	
		2 ኛ	1	200	76	100	46	56	
			2	190	70	80	43	50	

፲፫. የቤት እና አጥር ግንባታ ፈቃድ መስጠት (1742) የመጣኔ ማዕቀፍ

፩. ለመኖሪያ ቤት የግንባታ ፈቃድ ለመስጠት፣

፪. ነባር የመኖሪያ ቤት ህንፃ ላይ ወደ ጎን ተጨማሪ ክፍሎችን ለመገንባት ፈቃድ ለመስጠት፣

፫. የንግድና የቅይጥ አገልግሎት ህንፃ የግንባታ ፈቃድ ለመስጠት፣

፬. በነባር የንግድና የቅይጥ አገልግሎት ህንፃ ላይ ወደ ጎን ተጨማሪ ክፍሎችን ፈቃድ ለመስጠት፣

፭. ሪልስቴት (አፓርታማ) ግንባታ ፈቃድ ለመስጠት፣

፮. በነባር የሪልስቴት ህንፃ ላይ ወደ ጎን ተጨማሪ ክፍሎችን ፈቃድ ለመስጠት፣

፯. የትምህርት ተቋም፣ጤና ተቋም፣ለህክምና አገልግሎት መስጫ ህንፃ የግንባታ ፈቃድ ለመስጠት፣

፰. ለአምልኮ ቤት ህንጻ የግንባታ ፈቃድ ለመስጠት፣

፱. ለአስተዳደራዊ አገልግሎት ተቋም ህንፃ የግንባታ ፈቃድ ለመስጠት፣

፲. ለቀላል ኢንዱስትሪ (Light Industry) ተከላ ለሚሆን ህንፃ የግንባታ ፈቃድ ለመስጠት፣

፲፩. ለትልቅ/ከባድ ኢንዱስትሪ (Heavy or Noxious Industry)ተከላ የግንባታ ፈቃድ ለመስጠት፣

፲፪. ለተሽከርካሪ ጥገና ጋራዥ ግንባታ ፈቃድ ለመስጠት፣

፲፫. ለመኪና ማቆሚያ (Carport) የግንባታ ፈቃድ ለመስጠት፣

፲፬. የአጥር ግንባታ ፈቃድ ለመስጠት፣

፲፭. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፭) እስከ ንዑስ አንቀጽ (፲፬) ለሚሰጥ ፍቃድ በዚህ ሞዴል መመሪያ ሰንጠረዥ ሰባት በተሰጠው ማዕቀፍ መሠረት ይከፈላል።

ሠንጠረዥ ሰባት፦ ፕላን በማጽደቅ የግንባታ ፈቃድ ለመስጠት የመጣኔ ማዕቀፍ

ተ.ቁ	የአገልግሎት አይነት	መለኪያ		ፈርጅ አራት		ፈርጅ አምስት			
				መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳብ (ለፈርጅ አራት)	የውሳኔ ሃሳብ (ለፈርጅ አምስት)
1	**ፕላን ስምምነት ለመስጠት**	በፕላን	ብር	100	300	100	300	250	200
2	**ለመኖሪያ የግንባታ ፈቃድ**								
2.1	ፎቅ ቤት ከ(G+1- G+3)	በፎቅ ወለል	ብር	100	175	100	175	150	150
2.2	ፎቅ ቤት ከ(G+4- G+5)	በፎቅ ወለል	ብር	175	350	175	350	300	200
2.3	ፎቅ ያልሆነ እና ለሌሎች	በፍቃድ	ብር	100	200	100	200	200	200
3	**ለድርጅት ወይም ከመኖሪያ ቤት ውጪ የግንባታ ፈቃድ**								

ተ.ቁ	የአገልግሎት አይነት	መለኪያ		ፈርጅ አራት		ፈርጅ አምስት			
				መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳብ (ለፈርጅ አራት)	የውሳኔ ሃሳብ (ለፈርጅ አምስት)
3.1	ፎቅ ቤት ከ(G+1- G+3)	በፎቅ ወለል	ብር	275	550	275	550	350	300
3.2	ፎቅ ቤት ከ(G+4- G+5)	በፎቅ ወለል	ብር	563	1,125	563	1,125	700	550
3.3	ፎቅ ያልሆነ እና ለሌሎች	በፍቃድ	ብር	200	500	200	500	400	400
4	**ለሁሉም ፎቅ ቤት ከ G+5 በላይ የግንባታ ፈቃድ**	በፎቅ ወለል	ብር	600+100	1100+100	600+100	1100+100	800+100	700+50
5	**ለአጥር ሥራ ፈቃድ**	በፈቃድ	ብር	200	500	200	500	200	200

ማስታወሻ "**ለሁሉም** ፎቅ ቤት ከ G+5 **በላይ የግንባታ ፈቃድ +100"** ማለት በእያንዳንዱ ተጨማሪ ወለል 100 ብር በተጨማሪነት ይከፈላል። ማለት ነው።

፲፬. ከከተማ ቤት ጋር በተያያዘ ለሚሰጡ ሌሎች ፍቃድ **(1742)** የመጣኔ ማዕቀፍ

፮. አዲስ ለተገነባ ሕንፃ የመጠቀሚያ ፈቃድ ለመስጠት ከ 500 እስከ 2,000.00 ብር ይከፈላል።

፯. ለነባር ሕንፃ የአገልግሎት ለውጥ ወይም ማስፋፋት በማድረግ ለሚቀርብ ጥያቄ የመጠቀሚያ ፈቃድ ለመስጠት ከ 500 እስከ 2,000.00 ብር ይከፈላል።

፰. ሕንፃው ቅርጹን ወይም ይዘቱን ሳይቀይር የአገልግሎት ወይም የአጠቃቀም ለውጥ የማድረግ ፈቃድ ለመስጠት ከ 500.00 እስከ 2,000.00 ብር ይከፈላል።

፱. የሕንፃን ቅርጽ ወይም ይዘት በመቀየር (Through Remodeling) የአገልግሎት ወይም የአጠቃቀም ለውጥ የማድረግ ፈቃድ ለመስጠት ከ 1,000.00 እስከ 3,000.00 ብር ይከፈላል።

፲. የሕንፃን ቅርፅ ወይም ይዘት ለመቀየር (Remodeling) ፈቃድ ለመስጠት ከ 500.00 እስከ 2,000.00 ብር ይከፈላል።

፲፩. ለሕንፃ እድሳት ፈቃድ ለመስጠት ወይም ጊዚያዊ የግንባታ ፍቃድ ለመስጠት ከ 300.00 እስከ 1,000.00 ብር ይከፈላል።

፲፪. ለስቶር (Store) ግንባታ ፈቃድ ለመስጠት ከ 300.00 እስከ 1,000.00 ብር ይከፈላል።

፲፫. ለሼድ (Shed) ግንባታ ፈቃድ ለመስጠት ከ 300.00 እስከ 1,000.00 ብር ይከፈላል።

፲፬. ከግንባታ ሳይት ውጪ /Out of Construction Site/ ለሚሠራ ሼድ የግንባታ ፈቃድ ለመስጠት ከ 300.00 እስከ 1,000.00 ብር ይከፈላል።

፲፭. ግንባታን ለማፍረስ ፈቃድ ለመስጠት ከ 300.00 እስከ 1,000.00 ብር ይከፈላል።

፲፮. የምሽት ግንባታ ስራ ፍቃድ ለመስጠት ከ 300.00 እስከ 1,000.00 ብር ይከፈላል።

፲፯. ምትክ ማስረጃ ለመስጠት ከ 100.00 እስከ 500.00 ብር ይከፈላል።

<u>ማስታወሻ</u> ከዚህ በላይ በአንቀጽ (፲፬) የተመለከተው ናሙና የመጣኔ ተመን ከዚህ በታች በሰንጠረዥ ስምንት በተመለከተው ማዕቀፍ መሠረት ከተማው በተመደበበት ፊርጅ መነሻ በሚለይ የመጣኔ ተመን የሚተካ ይሆናል።

ሰንጠረዥ ስምንት:- ከከተማ ቤት ጋር በተያያዘ ለሚሰጡ ሌሎች የአገልግሎት ክፍያ የመጣኔ ማዕቀፍ

ተ.ቁ	የአገልግሎት አይነት	መለኪያ	ፈርጅ አራት		ፈርጅ አምስት			
			መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳብ(ለፈርጅ አራት)	የውሳኔ ሃሳብ(ለፈርጅ አምስት)
1	አዲስ ለተገነባው ሕንፃ የመጠቀሚያ ፈቃድ ለመስጠት።	ብር	500	1,000	500	1,000	700	600
2	ለነባር ሕንፃ የአገልግሎት ለውጥ ወይም ማስፋፋት በማድረግ ለሚቀርብ ጥያቄ የመጠቀሚያ ፈቃድ ለመስጠት	ብር	500	1,000	500	1,000	600	550
3	ሕንፃው ቅርጹን ወይም ይዘቱን ሳይቀይር የአገልግሎት ወይም የአጠቃቀም ለውጥ የማድረግ ፈቃድ ለመስጠት።	ብር	500	1,000	500	1,000	500	500
4	የሕንፃን ቅርጽ ወይም ይዘት በመቀየር (Through Remodeling) የአገልግሎት /የአጠቃቀም/ ለውጥ የማድረግ ፈቃድ ለመስጠት።	ብር	1,000	2,000	1,000	2,000	1000	1000
5	የሕንፃን ቅርፅ ወይም ይዘት ለመቀየር (Remodeling) ፈቃድ ለመስጠት							

ተ.ቁ	የአገልግሎት አይነት	መለኪያ	ፈርጅ አራት		ፈርጅ አምስት			
			መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳብ(ለፈርጅ አራት)	የውሳኔ ሃሳብ(ለፈርጅ አምስት)
		ብር	500	1,000	500	1,000	600	550
6	ለሕንፃ እድሳት ፈቃድ ለመስጠት ወይም ጊዜያዊ ግንባታ ፍቃድ	ብር	300	800	300	600	400	350
7	ለስቶር (Store) ግንባታ ፈቃድ ለመስጠት	ብር	300	800	300	600	400	300
8	ለሼድ (Shed) ግንባታ ፈቃድ ለመስጠት	ብር	300	800	300	600	400	300
9	ከግንባታ ሳይት ውጪ /Out of Construction Site/ ለሚሠራ ሼድ የግንባታ ፈቃድ ለመስጠት	ብር	300	800	300	600	450	300
10	ግንባታን ለማፍረስ ፈቃድ ለመስጠት	ብር	300	800	300	600	350	300
11	የምሽት ግንባታ ስራ ፍቃድ ለመስጠት	ብር	300	800	300	600	600	400
12	ምትክ ማስረጃ ለመስጠት	ብር	100	500	100	500	300	200

፲፭. የአፈር መድፊያ ፍቃድ **(1743)** በመንገድ ዳር /ክፍት ቦታ/ የሚሰጥ ፍቃድ

፩. በመንገድ ዳርቻ የግንባታ ማቴሪያል ለማራገፍ እና ከሐዘን ውጪ ድንኳን ለመትከል **የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል።**

፪. በመንገድ ዳርቻ ለቀይ መስቀል፣ በዘመቻ ለሚደረግ የጤና ምርመራና ክትባት እንዲሁም በመንግሰት ተቋማት፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት፣በበጎ አድራጎት ለሚከናወኑ ተመሳሳይ ተግባራት የሚተከሉ ድንኳኖች ከአገልግሎት ክፍያ ነፃ ናቸው።

፫. በመንገድ ዳር /ክፍት ቦታ/ ለሚሰጥ ፍቃድ **የመጣኔ ማዕቀፍ ዝርዝሩ በሰንጠረዥ ዘጠኝ ተመለክቷል።**

ሰንጠረዥ ዘጠኝ፡-የአፈር መድፊያ ፍቃድ እና ሌሎች የአገልግሎት ክፍያ የመጣኔ ማዕቀፍ

ተ ቁ	የአገልግሎቱ አይነት	መለኪያ	ፈርጅ አራት		ፈርጅ አምስት			
			መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳብ(ለፈርጅ አራት)	የውሳኔ ሃሳብ(ለፈርጅ አምስት)
1	አሸዋ፣ ድንጋይ፣ ጠጠር፣ እንጨት ማራገፊያ ፍቃድ በካሬ ሜትር በቀን (በአስፋልት መንገድ)	ብር	8	10	5	8	10	8
2	አሸዋ፣ ድንጋይ፣ ጠጠር፣ እንጨት ማራገፊያ ፍቃድ በካሬ ሜትር በቀን (ጌጠኛ መንገድ) ኮብል ስቶን	ብር	5	8	5	8	8	8
3	አሸዋ፣ ድንጋይ፣ ጠጠር ፣ እንጨት ማራገፊያ ፍቃድ በካሬ ሜትር በቀን (ጠጠርና ከዚያ በታች መንገድ)	ብር	4	8	4	8	8	8
4	የግንባታ አፈር ማራገፊያ	ብር	5	8	5	8	8	8

ተ ቁ	የአገልግሎቱ አይነት	መለኪያ	ፈርጅ አራት		ፈርጅ አምስት			
			መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳ ብ(ለፈር ጅ አራት)	የውሳኔ ሃሳብ(ለፈርጅ አምስት)
	ፍቃድ በካሬ ሜትር በቀን (በአስፋልት መንገድ)							
5	የግንባታ አፈር ማራገፊያ ፍቃድ በካሬ ሜትር በቀን (ጌጠኛ መንገድ) ኮብል ስቶን	ብር	3	8	3	8	5	5
6	የግንባታ አፈር ማራገፊያ ፍቃድ በካሬ ሜትር በቀን (ጠጠርና ከዚያ በታች መንገድ)	ብር	2	5	2	5	5	5
7	ከሐዘን ውጪ መንገድ ዳርቻ ድንኳን ለመትከል በቀን (በአስፋልት መንገድ)	ብር	40	80	30	60	50	30
8	ከሐዘን ውጪ መንገድ ዳርቻ ድንኳን ለመትከል በቀን (ጌጠኛ መንገድ) ኮብል ስቶን	ብር	30	60	30	60	40	30
9	ከሐዘን ውጪ መንገድ ዳርቻ ድንኳን ለመትከል በቀን (ጠጠርና ከዚያ በታች መንገድ)	ብር	20	50	20	50	40	30

ፒኗ. ከመሀንዲስ አገልግሎት **(1752)** የምህንድስና የአገልግሎት ክፍያ የመጣኔ ማዕቀፍ

፩. የምህንድስና አገልግሎት በቅየሣ ቦታ ለክቶ ለማስ ረከብ ለአንድ ጊዜ በሰንጠረዠ አስር

በተመለከተው ማዕቀፍ የሚወሰነው የመጣኔ ተመን ይከፈላል።

፪. ይዞታ ሲካፈል ወይም ይዞታ ሲቀላቀል በይዞታው ካሬ ሜትር መሠረት **በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የሚወሰነው የመጣኔ ተመን ይከፈላል።**

፫. የወሰን ድንጋይ ይተከልልኝ ወይም ይስተካከልልኝ የድንበር ግጭትን ወይም ክርክርን ለመፍታት 150 ብር **ይከፈላል።**

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጨማሪ ድንጋይ የሚያስፈልግ ከሆነ በአንድ ድንጋይ 40 ብር **ይከፈላል።**

ሠንጠረዥ አስር፡-የምህንድስና አገልግሎት የመጣኔ ማዕቀፍ

ተ ቁ	የከተማ ቦታ ይዞታ መጠን	መለኪያ	ፈርጅ አራት		ፈርጅ አምስት			
			መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳብ(ለፈርጅ አራት)	የውሳኔ ሃሳብ(ለፈርጅ አምስት)
1	እስከ 100 ካሬ ሜትር	ብር	190	210	180	200	200	180
2	101-200 ካሬ ሜትር	ብር	210	230	190	210	210	190
3	201-300 ካሬ ሜትር	ብር	290	310	270	290	300	280
4	301-400 ካሬ ሜትር	ብር	310	330	290	310	310	290
5	401-500 ካሬ ሜትር	ብር	390	410	370	390	400	370
6	ከ 501-1000 ካሬሜትር	ብር	410	430	390	410	410	390
7	ከ 1000 ካሬ ሜትር በላይ	ብር	720	740	700	720	720	700

፲፯. የሕንፃ ግንባታና ቁጥጥር አገልግሎት (1753) የመጣኔ ማዕቀፍ

፮. ለቤት ወይም ሕንፃ ግንባታ ለምድብ “ለ” ሕንፃ እና ለምድብ “ሐ” ሕንፃ ለሚደረግ የቁጥጥርና ክትትል ሥራ የአገልግሎት ክፍያ ይከፈላል።

፯. ለቤት ወይም ሕንፃ ግንባታ የቁጥጥርና ክትትል የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ በሰንጠረዥ

አስራ አንድ ተመላክቷል።

ሠንጠረዥ አስራ አንድ፦ ለሕንፃ ግንባታ ክትትልና ቁጥጥር የመጣኔ ማዕቀፍ

ተ.ቁ	የአገልግሎት አይነት	መለኪያ		ፊርጅ አራት		ፊርጅ አምስት			
				መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳብ(ለፊርጅ አራት)	የውሳኔ ሃሳብ(ለፊርጅ አምስት)
ሀ	**ለሕንፃ ግንባታ ቁጥጥር**								
1	ለመኖሪያ ፎቅ ቤት ከ (G+2- G+5)	ለአንድ ጊዜ	ብር	100	175	100	175	150	100
2	ለድርጅት ወይም ከመኖሪያ ቤት ውጪ								
2.1	ፎቅ ቤት ከ(G+1-G+3)	ለአንድ ጊዜ	ብር	125	250	125	250	200	150
2.2	ፎቅ ቤት ከ(G+4-G+5)	ለአንድ ጊዜ	ብር	275	550	275	550	300	275
3	**ለሁሉም** ፎቅ ቤት ከ **G+5 በላይ**	ለአንድ ጊዜ	ብር	600+100	1100+100	600+100	1100+100	600+100	600+100
ለ	**በሕንጻ ክትትልና ቁጥጥር**								
	የመስክ ሪፖርት የመሀንዲስ								

ተ.ቁ	የአገልግሎት አይነት	መለኪያ	ፈርጅ አራት		ፈርጅ አምስት			
			መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳብ(ለፈርጅ አራት)	የውሳኔ ሃሳብ(ለፈርጅ አምስት)
	አገልግሎት ሕንጻው ያረፈበት							
1	እስከ 100 ካሬ ሜትር	ለአንድ ጊዜ ብር	100	200	100	200	100	100
2	ከ 101-500 ካሬ ሜትር	ለአንድ ጊዜ ብር	175	350	175	350	200	200
3	ከ 501-1,000 ካሬ ሜትር	ለአንድ ጊዜ ብር	375	750	375	750	400	400
4	ከ 1,001-10,000 ካሬ ሜትር	ለአንድ ጊዜ ብር	750	1500	750	1500	800	800
5	ከ 10,001-50,000 ካሬ ሜትር	ለአንድ ጊዜ ብር	1250	2500	1250	2500	1250	1250
6	ከ 50,001-100,000 ካሬ ሜትር	ለአንድ ጊዜ ብር	2500	5000	2500	5000	2500	2500
7	ከ 100,000 ካሬ ሜትር በላይ	ለአንድ ጊዜ ብ	3750	7500	3750	7500	3750	3750

ተ.ቁ	የአገልግሎት አይነት	መለኪያ		ፊርጅ አራት		ፊርጅ አምስት			
				መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳብ(ለፊርጅ አራት)	የውሳኔ ሃሳብ(ለፊርጅ አምስት)
			ር						
8	የፍርድ ቤት አገልግሎት				በነጻ		በነጻ	በነጻ	በነጻ
9	አቤቱታና ቅሬታ ለሚያጣራ አካል				በነጻ		በነጻ	በነጻ	በነጻ

<u>ማስታወሻ</u> **ለሁሉም** ፎቅ ቤት ከ **G+5 በላይ+100** በእያንዳንዱ ተጨማሪ ወለል 100 ብር በተጨማሪነት ይከፈላል።

፲፰. የዲዛይን ጥናት፣ የዋጋና የጨረታ ሰነድ ዝግጅት አገልግሎት **(1754)** የመጣኔ ማዕቀፍ

፩. ለፕላን ወይም ዲዛይን ጥናትና ዋጋ ዝርዝር ዝግጅት

ሀ) እስከ አንድ ሚሊዮን ብር የግንባታ ዋጋ ግምት ለሚኖራቸው 0.1 በመቶ ይከፈላል።

ለ) ከአንድ ሚሊዮን እስከ ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር የግንባታ ዋጋ ግምት ለሚኖራቸው 0.08 በመቶ ይከፈላል።

ሐ) ከሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን እስከ አምስት ሚሊዮን ብር የግንባታ ዋጋ ግምት ለሚኖራቸው 0.066 በመቶ ይከፈላል።

መ) ከአምስት ሚሊዮን እስከ አስር ሚሊዮን ብር የግንባታ ዋጋ ግምት ለሚኖራቸው 0.058 በመቶ ይከፈላል።

ሠ) ከአስር ሚሊዮን በላይ የግንባታ ዋጋ ግምት ለሚኖራቸው 0.005 በመቶ ይከፈላል።

፪. ለጨረታ ሰነድ ዝግጅትና ጨረታ ማካሄድ

ሀ) እስከ አንድ ሚሊዮን ብር የግንባታ ዋጋ ግምት ለሚኖራቸው 0.025 በመቶ ይከፈላል።

ለ) ከአንድ ሚሊዮን እስከ ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር የግንባታ ዋጋ ግምት ለሚኖራቸው 0.02 በመቶ ይከፈላል።

ሐ) ከሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን እስከ አምስት ሚሊዮን ብር የግንባታ ዋጋ ግምት ለሚኖራቸው 0.0165 በመቶ ይከፈላል።

መ) ከአምስት ሚሊዮን እስከ አስር ሚሊዮን ብር የግንባታ ዋጋ ግምት ለሚኖራቸው 0.029 በመቶ ይከፈላል።

ሠ) ከአስር ሚሊዮን በላይ የግንባታ ዋጋ ግምት ለሚኖራቸው 0.0125 በመቶ የጨረታ ሰነድ ዝግጅትና ጨረታ ማካሄድ ይከፈላል።

፫. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተመለከተው የአገልግሎት ክፍያ ስሌት ከዚህ በታች በተመለከተው ሰንጠረዥ አስራ ሁለት በየደረጃው በሚያርፈው የገንዘብ መጠን ግብር በማስላት ክፍያ ይፈጸማል።

ሠንጠረዥ አስራ ሁለት፦ የዲዛይን ጥናት፣ የዋጋና የጨረታ ሰነድ ዝግጅት አገልግሎት ክፍያ

ተ.ቁ	የግንባታ ዋጋ ግምት	የሚወሰደው የገንዘብ መጠን	ለፕላን ወይም ዲዛይን ጥናትና ዋጋ ዝርዝር ዝግጅት		ለጨረታ ሰነድ ዝግጅትና ጨረታ ማካሄድ	
			መጣኔ ተመን በመቶኛ	የክፍያ መጠን	መጣኔ ተመን በመቶኛ	የክፍያ መጠን
1	እስከ አንድ ሚሊዮን ብር	1,000,000.00	0.10	1,000.00	0.025	250.00
2	ከአንድ ሚሊዮን በላይ እስከ ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር	1,500,000.00	0.08	1,200.00	0.02	300.00
3	ከሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን እስከ አምስት ሚሊዮን ብር	2,500,000.00	0.066	1,650.00	0.0165	412.50
4	ከአምስት ሚሊዮን እስከ አስር ሚሊዮን ብር	5,000,000.00	0.058	2,900.00	0.0145	725.00
5	ከአስር ሚሊዮን በላይ	ቀሪ 25,000,000.00 ብር በዚህ ማዕቀፍ ይወድቃል	0.05	12,500.00	0.0125	3,125.00
	የ 35,000,000.00 ብር ግምት የሚኖረው ክፍያ			19,250.00		4,812.50

፲፱. የፕላን መገምገሚያ የአገልግሎት ክፍያ **(1754)** የመጣኔ ማዕቀፍ

፳. ለሁሉም የሕንጻ ምድቦች የፕላን መገምገሚያ ክፍያ ይከፈላል።

፳፪. ለግንባታ ጥቅም ላይ የሚውሉት ፕላኖች በማዘጋጃ ቤት ተዘጋጅተው የሚሰጡ ስታንዳርድ ፕላኖች ከሆኑ ፕላኖቹን ለማግኘት የሚፈጸመው ክፍያ እንደ ፕላን መገምገሚያ ክፍያ ይቆጠራል።

፫. የኘላን መገምገሚያ ክፍያ የፕሮጀክት ግምት የሚሰላው የቤቱ ወይም የሕንጻው ጠቅላላ የወለል ስፋት ሲባዛ የግንባታ ወጪ በካሬ ሜትር ይሆናል።

፬. የፕሮጀክቱ ግምት እስከ 2,500,000.00 ብር ለሚሆን (የፕሮጀክቱ ግምት x 0.05 በመቶኛ) የፕላን መገምገሚያ ክፍያ ይከፈላል።

፭. የፕሮጀክቱ ግምት ከብር ከ 2,500,000.00 እስከ 5,000,000.00 ለሚሆን (የፕሮጀክቱ ግምት- 2,500,000.00) x (0.04 በመቶኛ) + 1,250.00 የፕላን መገምገሚያ ክፍያ ይከፈላል።

፮. የፕሮጀክቱ ግምት ከብር 5,000,000.00 እስከ 10,000,000.00 ለሚሆን (የፕሮጀክቱ ግምት- 5,000,000.00) x (0.033 በመቶኛ) + 2,250.00 የፕላን መገምገሚያ ክፍያ ይከፈላል።

፯. የፕሮጀክቱ ግምት ከብር 10,000,000.00 እስከ 20,000,000.00 ለሚሆን (የፕሮጀክቱ ግምት- 10,000,000.00) x (0.029 በመቶኛ) + 3,916.67 የፕላን መገምገሚያ ክፍያ ይከፈላል።

፰. የፕሮጀክቱ ግምት ከብር 20,000,000.00 እስከ 50,000,000.00 ለሚሆን (የፕሮጀክቱ ግምት- 20,000,000.00) x (0.025 በመቶኛ) + 6,777.14 የፕላን መገምገሚያ ክፍያ ይከፈላል።

፱.የፕሮጀክቱ ግምት ከብር 50,000,000.00 በላይ ለሚሆን (የፕሮጀክቱ ግምት-50,000,000.00) x (0.02 በመቶኛ) + 14,270.00 የፕላን መገምገሚያ ክፍያ ይከፈላል።

፲. ውድቅ የሆኑ ፕላኖች ተስተካክለው እንደገና ለማፀደቅ በሚቀርቡበት ጊዜ የፕላን መገምገሚያው ክፍያ ለምድብ "ሀ" ሕንፃ የመጀመሪያውን ክፍያ ግማሽ እና ለምድብ "ለ" እና "ሐ" ሕንፃ የመጀመሪያውን ክፍያ 25 በመቶ ይሆናል።

፲፩. ፕላኑ ውድቅ የተደረገበት ምክንያት ቀደም ሲል ይኸው ፕላን ግምገማ በተደረገበት ጊዜ ሳይታይ በታለፈ ግድፈት ምክንያት ከሆነ ተስተካክሎ የሚቀርበው ፕላን ለመገምገም ክፍያ አይጠየቅም።

፲፪. የፕላን ማሻሻያ ክፍያ /Plan Modification/ ስትራክቸራል ፕላኑን እንዲለውጥ የሚያስገድድ ከሆነ ክፍያው በአዲስ ፕላን መገምገሚያ አከፋፈል መሠረት ይሆናል።

፲፫. ለማሻሻያ የሚከፈለው የፕላን መገምገሚያ ክፍያ ለአዲስ ፕላን መገምገሚያ የሚጠየቀው ክፍያ 25 በመቶ ይከፈላል።

፭. የስም ዝውውር አገልግሎት

፩. የስም ዝውውር የተሻሻለው የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 135/2003 ዓ.ም መሠረት የሚከፈለው ክፍያ፣

፪. በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 እንደተሻሻለው እና በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 57/1995 መሠረት ከታክስ ነፃ ከተደረገው ውጪ የሚከፈለው ክፍያ፣

፫. የካፒታል ሀብቶች በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ግብር የሚወሰንበት መመሪያ ቁጥር 48/2014 መሠረት የሚከፈለው ክፍያ፣

፬. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፫) የሚከፈለው ክፍያ እንደተጠበቀ ሆኖ አሹራ ማረጋገጫ ለመስጠት በአንቀጽ (፯፩) እና የውል ምዝገባና ማስረጃ አገልግሎት ለመስጠት በአንቀጽ (፯፪) በተደነገገው መሠረት ክፍያዎች የተፈጸሙ መሆናቸው ሲረጋገጥ የስም ዝውውሩ ይካሄዳል።

፯፩. አሹራ ማረጋገጫ ከመስጠት (1702) የመጣኔ ማዕቀፍ

፩. የሽያጭ እና የስጦታ ተዋዋይ ወገኖች የውል ሰነድ የአካባቢውን የወቅቱ የገበያ ዋጋ የማያመላክት ከሆነ የግንባታ ወጪ ግምት መነሻ በመውሰድ የቤቱ ወይም የሕንጻው የገበያ ዋጋ የአሹራ ሁለት በመቶ ይከፈላል።

፪. የድርሻ መልቀቅ ተዋዋይ ወገኖች የውል ሰነድ የገበያ ዋጋ ላይ የአሹራ ሁለት በመቶ ይከፈላል።

፫. ከግለሰብ ወደ ንግድ ማህበራት ወይንም ከንግድ ማህበር ወደ ግለሰብ ይዞታ የስም ዝውውር የውል ሰነድ ወይም የገበያ ዋጋ የተሻለው ላይ የአሹራ ሁለት በመቶ ይከፈላል።

፬. የመኖሪያ ቤት የሕብረት ስራ ማህበራት አባላትን በመተካት የሚፈፀም ዝውውር ከገበያ ዋጋ የአሹራ ሁለት በመቶ ይከፈላል።

፭. ከባል ወደ ሚስት ወይም ከሚስት ወደ ባል ዝውውር ከሌላው ድርሻ ላይ ከቤቱ ወቅታዊ የግንባታ ዋጋ አንድ በመቶ ይከፈላል።

፮. የድርጅቶች መዋሃድ ወይም መከፋፈል የውል ሰነድ የግንባታ ዋጋ ላይ የአሹራ አንድ በመቶ ይከፈላል።

፯፪. የውል ምዝገባ ማስረጃ አገልግሎት (1755) የመጣኔ ማዕቀፍ

፩. ሊዝ የመጠቀም መብትን ለማዛወር ሊዝ መብት ማስተላለፊያ ዋጋ ላይ ሁለት ነጥብ አምስት በመቶ

የስም ዝውውር ይከፈላል።

፪. በፍርድ አፈጻጸም እና በፋይናንስ ተቋም በሃራጅ ሽያጭ ዋጋ ላይ ሁለት በመቶ የስም ዝውውር ይከፈላል።

፫. በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ የተላለፈ ይዞታ ከግንባታው ዋጋ ሁለት በመቶ የስም ዝውውር ይከፈላል።

፬. በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የሚሸጥ ይዞታ የስም ዝውውር በሽያጭ ዋጋ ላይ ሁለት በመቶ ይከፈላል።

፭. በፍርድ ቤት የተረጋገጠ በውርስ የሚተላለፍ የስም ዝውውር በቁርጥ አንድ ሺህ ብር ይከፈላል።

፮. ከመኖሪያ ቤት ወደ ንግድ አገልግሎት ዝውውር ከቤቱ ወቅታዊ የግንባታ ዋጋ አንድ በመቶ ይከፈላል።

፯. ለማኛውም ውል በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ ፩ እስከ ፮ ከተገለጸው ውጪ የሚቀርብ የውል ምዝገባ በማዘጋጃ ቤቱ ባለሙያ ግምት ወይም በውል ላይ ከተመለከተው ዋጋ በተሻለው ላይ ሁለት በመቶ ይከፈላል።

፰. በአንቀጽ ፶፩ እና ፶፪ በተገለጸው መሠረት ዝውውሩን ለማጠናቀቅ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለማዘጋጀት በአንቀጽ (፶፩) ንዑስ አንቀጽ (፩ እና ፪) የተመለከተው ክፍያ ይፈጸማል።

፱. በአንቀጽ ፶፩ እና ፶፪ በተገለጸው መሠረት ዝውውሩን ለማጣራት በቅድሚያ በአንቀጽ (፲፯) የመሀንዲስ አገልግሎት ክፍያ በይዞታው መጠን ልክ መክፈል ይኖርበታል።

፶፫. የቦታ ማግኘት ምዝገባ አገልግሎት **(1773)** የመጣኔ ማዕቀፍ

፩. **በምደባ ወይም በሌሎች አማራጭ ቦታ ለማግኘት ለሚካሄድ ምዝገባ ከ** 150-200 **ብር ይከፈላል።**

፪. **ለመኖሪያ ቤት በሊዝ ለሚቀርብ ቦታ የጨረታ ዶክመንት ሽያጭ ከ** 300-400 **ብር ይከፈላል።**

፫. **ከመኖሪያ ቤት ውጪ ለንግድ፣ለኢንቨስትመንት..ወዘተ የጨረታ ዶክመንት ሽያጭ ከ** 400-500 **ብር ይከፈላል።**

፶፬. የመሬት ይዞታ ካርታ፣የቤት ባለቤትነት ደብተር፣ የካርታ እድሳትና የቤት አገልግሎት **(1774)** ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እና ምትክ ማስረጃ መስጠት የመጣኔ ማዕቀፍ

፮. የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመጀመሪያ ጊዜ ለማዘጋጀት የሁለት ሰርተፊኬት (ዋና እና ኮፒ)

የህትመት ዋጋ 300 ብር ይከፈላል።

፯. በሰርተፍኬት ወረቀት ላይ የይዞታው ስዕላዊ መግለጫና ሌሎች መረጃዎች ለማዘጋጀት ብር 100

ይከፈላል፣

፰. የተበላሸ ሰርተፊኬትን በባለይዞታው ጥያቄ ለመተካት የተበላሸውን በማስወገድ የሁለት ሰርተፊኬት

የህትመት ዋጋ 300 ብር እና ስዕላዊ መግለጫ ለማዘጋጀት ብር 100 ይከፈላል።

፱. የጠፋ ሰርተፍኬት ከሆነ የማስታወቂያ ወጪ በሀገር አቀፍ ሽፋን ባለው ጋዜጣ የሚታወጅበትን

በግለሰቡ አማካኝነት የህትመት ድርጅቱ የሚወስነው ክፍያ የሚፈጸም ሆኖ በአካባቢ ለሚወጣው

ማስታወቂያ ከ 50 እስከ 100 ብር ይከፈላል እንዲሁም የሁለት ሰርተፊኬት የህትመት ዋጋ 300 ብር

እና ስዕላዊ መግለጫ ለማዘጋጀት ብር 100 ይከፈላል።

፲. ይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ላላቸውም ሆነ ለሌላቸው ሰነድ ማጣሪያ 500 ብር በሰርተፍኬት

ይከፈላል።

፲፩. የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ህጋዊነት ማረጋገጫ ጀርባ ማህተም 600 ብር በሰርተፍኬት

ይከፈላል።

፲፪. የግንባታ ዲዛይን/ፕላን መረጃ /ኮፒ /ቅጂ/ብሉ ፕሪንት ለመስጠት 200 ብር በፕላን ይከፈላል።

፲፫. እዳና እገዳ ምዝገባና ስረዛ፤ ለሀራጅ ትዕዛዝ ባለሙያ ለመላክ (1775) የመጣኔ ማዕቀፍ

፩. ባንክ ወይም ሌላ አካል በዋስትና ንብረት ለመያዝ የባለቤትነት ማስረጃ በሰነድ ላይ ያለው እና የይዞታው መጠን በቦታው የሚገኝ መሆኑን ለማረጋገጥ (የማህደር ማጣሪያ) 500 ብር ይከፈላል።

፪. ከባንክ፣ ከኢንሹራንስ እና ሌሎች በህግ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት የዕግድ ምዝገባ የአገልግሎት

ክፍያ ብር 200 በብድር ዘመኑ ተባዝቶ የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል።

፫. ለሃራጅ ትዕዛዝ ባለሙያ ለመላክ የአገልግሎት ክፍያ 600 ብር ይከፈላል።

፬. ዕገዳውና ዋስትናው እንዲሰረዝ በዕግድ ከያዘው አካል ደብዳቤ ወይም ማስረጃ ሲቀርብ ወይም

የእገዳው ጊዜ ገደብ ሲያበቃ ዕገዳውን ከመዝገብ ላይ ለመሰረዝ እና ዕገዳው የተነሳ ስለመሆኑ

ለሚመለከታቸው አካላት በደብዳቤ ለማሳወቅ የአገልግሎት ክፍያ ብር 100 ይከፈላል።

፯. ለፍርድ ቤት ለግለሰብ ዋስትና ለማስያዝ ብር 150 ይከፈላል።

፮. በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል እና በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ማገድና ማንሳት ከአገልግሎት ክፍያ ነፃ ናቸው።

፳፯. ከሚለጠፍ፣ ከሚንጠለጠል፣ ከሚተከል እና በማንኛውም መንገድ የማስተዋወቅ ሥራ

(1782) የመጣኔ ማዕቀፍ

፩.የንግድ ወይም የመለያ ምልክቶችን በተፈቀዱ ቦታዎች ላይ ከሚለጠፍ፣ ከሚንጠለጠል፣ ከሚተከል እና በማንኛውም መንገድ የማስተዋወቅ ተግባር ከሚፈጽም ማንኛውም ሰው የውጭ ማስተዋወቅ ህጋዊነትን ለማረጋገጥ ይዘትና አቀራረብን በማጣራት ለሚሰጥ ፍቃድ የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል።

፪. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማስታወቂያ አዋጅ ቁጥር 759/2004 አንቀጽ (36) ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን በንዑስ አንቀጽ (3) ክልሎች የውጭ ማስታወቂያን በሚመለከት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችንና መመሪያዎችን ሊያወጡ ይችላሉ። በሚለው ድንጋጌ የውጭ ማስተዋወቅ ደንብ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ የኮንስትራክሽን ባለስልጣን በኩል በማዘጋጀትና በማጸደቅ የአገልግሎት ክፍያዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

፫. ማንኛውም ሰው የውጭ ማስተዋወቅ ሥራ ከማካሄዱ በፊት ለማስታወቂያ ሰሌዳ ተከላና የማስተዋወቅ ተግባር ለማካሄድ ከማዘጋጃ ቤት ፈቃድ ማግኘትና የተመዘገበ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ መያዝ አለበት።

፬. በዚህ መመሪያ መነሻ በወረዳ ምክር ቤት መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የውጭ ማስተዋወቅ ሥራ የጀመረ ማንኛውም ሰው በከተማ ወይም ወረዳ ምክር ቤት መመሪያ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በጽሑፍ ለማዘጋጃ ቤት በማመልከት ፍቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) በተገለጸው አግባብ ፍቃድ ያላገኘ ህገ-ወጥ የውጭ ማስተዋወቅ ተግባር ቅጣት ይከፍላል።

፮. የከተማን መሬት ወይም ሕንፃን ለተወሰነ ጊዜ ለውጭ ማስተዋወቅ ሥራ የሚገለገል ማንኛውም

ሰው የአገልግሎት ክፍያ ይፈጽማል።

፮. የመንግስት መሥሪያ ቤቶች፣ የኃይማኖት ተቋማት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ለትርፍ ያልተቋቋሙ

የዲፕሎማቲክ ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ማንኛውም ሰው

ስለ ኤች አይቪ/ኤድስ እና ኮቪድ (19) አስተምሮት ከውጭ ማስተዋወቅ የአገልግሎት ክፍያ ነፃ ናቸው።

፯. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአካባቢያቸው እና በንብረታቸው ላይ የተገደበ ነው።

፱. ማንኛውም ሰው የውጭ ማስተዋወቅ ሥራ ለማቋረጥ ወይም ማስታወቂያውን ለማንሳት በጽሑፍ ማሳወቅ እና ማስታወቂያው እስከ ተነሳበት ቀን ድረስ የሚፈለግበትን የአገልግሎት ክፍያ መክፈል ይኖርበታል።

፲. **የውጭ የማስተዋወቅ *ሥራ* የአገልግሎት ክፍያ** በሠንጠረዥ አስራ ሦስት በዝርዝር ተመላክቷል።

ሠንጠረዥ አስራ ሦስት ፦ የውጭ የማስተዋወቅ ሥራ የአገልግሎት ክፍያ

ተ.ቁ	የአገልግሎት አይነት	መለኪያ		ፈርጅ አራት		ፈርጅ አምስት			
				መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳብ (ለፈርጅ አራት)	የውሳኔ ሃሳብ (ለፈርጅ አምስት)
ሀ	**የውጭ ማስታወቂያ ሀጋዊነትን ማረጋገጥ**								
1	እስከ 16 ካሬ ሜትር	ካሬ ሜትር	ብር	400	1,250	400	1,250	400	400
2	ከ 16-36 ካሬ ሜትር	ካሬ ሜትር	ብር	800	2,000	800	2,000	800	800
3	ከ 36 ካሬ ሜትር በላይ	ካሬ ሜትር	ብር	1,500	3,700	1,500	3,700	1500	1500
ለ	**ሀገ ወጥ የውጭ ማስተዋወቅ ቅጣት**								
1	እስከ 16 ካሬ ሜትር	ካሬ ሜትር	ብር	500	1,500	500	1,500	500	500
2	ከ 16-36 ካሬ ሜትር	ካሬ ሜትር	ብር	1,000	2,500	1,000	2,500	1000	1000
3	ከ 36 ካሬ ሜትር በላይ	ካሬ ሜትር	ብር	2,000	4,000	2,000	4,000	2000	2000
ሐ	**የውጭ ማስተዋወቅ ሥራ የአገልግሎት ክፍያ**								

ተ.ቁ	የአገልግሎት አይነት	መለኪያ		ፊርጅ አራት		ፊርጅ አምስት			
				መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳብ (ለፊርጅ አራት)	የውሳኔ ሃሳብ (ለፊርጅ አምስት)
1	በግል ይዞታ/ሕንጻ ወይም በአጥር ላይ የሚለጠፍ ወይም የሚጻፍ								
	በነጠላ	በሜትር ካሬ	በዓመት ብር	150	300	150	300	150	150
	በሁሉም ገጽ	በሜትር ካሬ	በዓመት ብር	275	550	275	550	300	275
2	በግል ይዞታ/በጠያቂው ይዞታ ውስጥ በቋሚ ምሰሶ የሚተከል			-		-			
	በነጠላ	በሜትር ካሬ	በዓመት ብር	150	300	150	300	200	150
	በሁሉም ገጽ	በሜትር ካሬ	በዓመት ብር	275	550	275	550	300	275
3	በግል/የራሱ ባልሆነ ይዞታ ውስጥ በቋሚ ምሰሶ የሚተከል								
	በነጠላ	በሜትር ካሬ	በዓመት ብር	275	550	275	550	300	275
	በሁሉም ገጽ	በሜትር ካሬ	በዓመት ብር	350	700	350	700	400	350
4	በአመልካቹ ይዞታ ውስጥ ያለን ተቋም ለማስተዋወቅ ተቋሙ ባለበት	በሜትር ካሬ	በዓመት ብር	3,7	7,5	3,7	7,500	3750	3750

ተ.ቁ	የአገልግሎት አይነት	መለኪያ		ፊርጅ አራት		ፊርጅ አምስት			
				መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳብ (ለፊርጅ አራት)	የውሳኔ ሃሳብ (ለፊርጅ አምስት)
	ይዞታ ውስጥ የሚተከል ሰሌዳ			50	00	50			
5	በሕንጻ አናት ላይ የሚተከል			-		-			
	በነጠላ	በሜትር ካሬ	በዓመት ብር	275	550	275	550	275	275
	በሁሉም ገጽ	በሜትር ካሬ	በዓመት ብር	350	700	350	700	400	350
6	በማንኛውም የትራንስፖርት ተሸከርካሪ የውጭ አካል ላይ የሚለጠፍ	በሜትር ካሬ	በዓመት ብር	150	300	150	300	200	200
7	በሚሰጥ ቦታ ላይ ቢል ቦርድ ማቆም								
	በነጠላ	በሜትር ካሬ	ወርሃዊ/ ዓመታዊ		በጨረታ		በጨረታ		
	በሁሉም ገጽ	በሜትር ካሬ	ወርሃዊ/ ዓመታዊ		በጨረታ		በጨረታ		
8	የከተማ አስተዳደሩ በሆኑ ንብረቶች ላይ የሚለጠፍ ወይም የሚተከል								

ተ.ቁ	የአገልግሎት አይነት	መለኪያ		ፈርጅ አራት		ፈርጅ አምስት			
				መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳብ (ለፈርጅ አራት)	የውሳኔ ሃሳብ (ለፈርጅ አምስት)
	በነጠላ	በሜትር ካሬ	ወርሃዊ/ዓመታዊ		በጨረታ		በጨረታ		
	በሁሉም ገጽ	በሜትር ካሬ	ወርሃዊ/ዓመታዊ		በጨረታ		በጨረታ		
9	በማንኛውም ቦታ የሚተከል ተለዋዋጭ ገጽ ያለው የውጭ ማስታወቂያ	በሜትር ካሬ	በዓመት ብር	750	1,500	750	1,500	750	750
10	በማንኛውም ቦታ የሚተከል በብርሃን፣ በምስልና ድምጽ ወይም በዲጅታል ቴክኖሎጂ የሚታይ የውጭ ማስታወቂያ	በሜትር ካሬ	በዓመት ብር	1,000	2,000	1,000	2,000	1000	1000
11	በማንኛውም ቦታ በሦስት ምስል ማስታወቂያ	በሜትር ካሬ	በዓመት ብር	1,000	2,000	1,000	2,000	1000	1000
12	በግድግዳና ጣሪ ላይ የሚሳል ማስታወቂያ	በሜትር ካሬ	በዓመት ብር	1,250	2,500	1,250	2,500	1250	1250
13	በአውቶቢስ ፌርማታ፣በቆሻሻ ማጠራቀሚያ፣በኾግኝ መትከያ	በሜትር ካሬ	በዓመት ብር	-	ጨረታ	-	ጨረታ		

ተ.ቁ	የአገልግሎት አይነት	መለኪያ		ፈርጅ አራት		ፈርጅ አምስት			
				መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳብ (ለፈርጅ አራት)	የውሳኔ ሃሳብ (ለፈርጅ አምስት)
	የሚለጠፍ ማስታወቂያ								
14	በከተማ አስተዳደሩ በሚሰጥ ቦታ ላይ ተለጣፊ ጽሁፎችን፣ ፖስተሮችንና የወረቀት ማስታወቂዎችን መለጠፊያ ቦርድ ማቆም								
	በነጠላ	በሜትር ካሬ	በዓመት ብር	-	ጨረታ	-	ጨረታ		
	በሁሉም ገጽ	በሜትር ካሬ	በዓመት ብር	-	ጨረታ	-	ጨረታ		
15	ተንጠልጣይ ነገሮች/ባነር/	በሜትር ካሬ	በቀን ብር	15	30	15	30	20	20
	የሚለጠፉ ፖስተሮች	በቁጥር	አንድ ጊዜ ብር	1.25	2.5	1.25	2.5	1.25	1.25
16	በተተከሉ ወይም በቆሙ ነገሮች ላይ የሚለጠፉ ፖስተሮች	ብዛቱ ከ200 ያለነሰ ሆኖ በገጽ	አንድ ጊዜ ብር	0.15	0.3	0.15	0.3	0.3	0.3
17	የተባዙ በራሪ ወረቀት ማስታወቂያዎች (ሊፋሌት፣ ብሮሸር፣ ፍላየር፣ ወረቀት ወይም መሰል ማስታወቂያ)	ብዛቱ ከ200 ያለነሰ ሆኖ በገጽ	አንድ ጊዜ ብር	0.1	0.15	0.1	0.15	0.15	0.15
18	የሚለጠፍ የስቲከር ማስታወቂያ	ብዛቱ ከ50 ያለነሰ ሆኖ በገጽ	አንድ ጊዜ ብር	1.25	2.5	1.25	2.5	2.5	

ተ.ቁ	የአገልግሎት አይነት	መለኪያ		ፊርጅ አራት		ፊርጅ አምስት			
				መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳብ (ለፊርጅ አራት)	የውሳኔ ሃሳብ (ለፊርጅ አምስት)
19	በድምጽ ማጉያ መሳሪያ ወይም በድምጽ ካሴት የሚሰራጭ ማስታወቂያ	በተሰራጨበት ሰዓት	ስርጭቱ በተካሄደበት ሰዓት መጠን ብር	250	500	250	500	250	250
20	የበረንዳ ጥላ፣ በፊርማታ፣ነዳጅ ማደያና ሌሎች መሰል ማስታወቂያዎች	በቁጥር	አንድ ጊዜ ብር	100	300	100	300	100	100
21	በአየር ላይ የሚንሳፈፍ ፊኛና መሰል ማስታወቂያ	በቁጥር	አንድ ጊዜ ብር	100	300	100	300	100	100
22	ጊዚያዊ የህንጻ ኪራይ ወይም ሽያጭንና መሰል ማስታወቂያ	በቁጥር	አንድ ጊዜ ብር	100	300	100	300	100	100
23	ለአጭር ጊዜ የሚቆዩ የተለያዩ ማስታወቂያዎች								
	1ኛ ደረጃ ቦታ ማስታወቂያዎች	በካሬ ሜትር በወር)	ብር	8	10	8	10	8	8
10	2ኛ ደረጃ ቦታ ማስታወቂያዎች	በካሬ ሜትር በወር)	ብር	5	10	5	10	10	10

ተ.ቁ	የአገልግሎት አይነት	መለኪያ		ፊርጅ አራት		ፊርጅ አምስት			
				መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳብ (ለፊርጅ አራት)	የውሳኔ ሃሳብ (ለፊርጅ አምስት)
	3ኛ ደረጃ ቦታ ማስታወቂያዎች	በካሬ ሜትር በወር)	ብር	3	5	3	5	5	5
24	ለማንኛውም የማስታወቂያ ሰሌዳ ፍቃድ	በካሬ ሜትር	አንድ ጊዜ ብር	30	50	30	50	30	30
25	የቅጥርና ሌሎች ማስታወቂያዎች ለመለጠፍ	በማስታወቂያ ሰሌዳ	አንድ ጊዜ ብር	3	8	3	8	5	5
26	የንግድ ትርኢትና ባዛር ፈቃድ	በፈቃድ	ብር	300	500	300	500	300	300
27	የንግድ ትርኢትና ባዛር አገልግሎት በመንግስት ይዞታ በቀን /አዘጋጅ/	በቀን	ብር	100	150	50	100	100	100
28	የንግድ ትርኢትና ባዛር/ ምርት እና አገልግሎት ለማስተዋወቅ /ተሳታፊ/	በቀን	ብር	50	80	30	50	50	30

፸፯. ሌሎች ዕቃዎችና አገልግሎቶች **(1789)** የመጣኔ ማዕቀፍ

፩. ማስረጃ ለጠፋባቸዉ ምትክ መረጃ ለመሰጠት ከ 20 እስከ 50 ብር ይከፈላል።

፪. የመረጃ ኮፒ መስጠት ለመጀመሪያው አንድ ገጽ 25 ብር ለተጨማሪ ለእያንዳንዱ ሰነድ 3 ብር ይከፈላል።

፫. ለተለያዩ ተቋማት ድጋፍ ደብድቤ ለመጻፍ ለመጠጥ ውሃ፣ ለቴሌ፣ለመብራት...ወዘተ በደብዳቤ ከ 80 እስከ 100 ብር ይከፈላል።

፬. ከፍርድ ቤት እና ከመንግስት ተቋማት ለሚጠየቁ መረጃዎች ኮፒ ለመስጠት ከአገልግሎት ክፍያ ነፃ ናቸው።

፸፰. ከደንብ መተላለፍ ቅጣት **(1746)** ህግን በመተላለፍ ወይም ባለመጠበቅ የሚጣል መቀጫ፤

፩. በወንጀልና የፍታብሔር ህግ የተደነገጉ የጥፋተኝነት ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ደንብና መመሪያ በሚተላለፍ የግንባታ ባለቤት ላይ አስተዳደራዊ መቀጫ ይከፈላል።

፪. ፍቃድ የተሰጠበት ፕላን ማመልከቻ ኮፒ በግንባታ ቦታ አለመገኘት ምድብ (ለ) ሕንፃ ብር 2,000.00 እና ምድብ (ሐ) ሕንፃ ብር 3,000.00 ይከፈላል።

፫. የውስጥ አደረጃጀት ወይም የግንባታ ቅደመ ዝግጅት ሳይሟለ ሥራ መጀመር ምድብ (ለ) ሕንፃ ብር 2,000.00 እና ምድብ (ሐ) ሕንፃ ብር 3,000.00 ይከፈላል።

፬. የተሰጡ የማስተካከያ ትእዛዞችን ካጠናቀቁ በኋላ አለማስታወቅ ምድብ (ሀ) ሕንፃ ብር 1,000.00፣ ምድብ (ለ) ሕንፃ ብር 2,000.00 እና ምድብ (ሐ) ሕንፃ ብር 3,000.00 ይከፈላል።

፭. የተሰጡ ትእዛዞችን በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ አለማከናወን ምድብ (ሀ) ሕንፃ ብር 1,000.00፣ ምድብ (ለ) ሕንፃ ብር 2,000.00 እና ምድብ (ሐ) ሕንፃ ብር 2,000.00 ይከፈላል።

፮. ከግንባታ ክልል ውጪ የተቀመጠን የግንባታ ቁሳቁስ ወይንም ተረፈ ምርት በሚሰጥ የጽሁፍ ማስታወቂያ መሠረት አለማንሳት ምድብ (ሀ) ሕንፃ ብር 1,000.00 ምድብ (ለ) ሕንፃ ብር፣ 2,000.00 እና ምድብ (ሐ) ሕንፃ ብር 3,000.00 ይከፈላል።

፯. ያለተቆጣጣሪ መሐንዲስ ሕንፃ ማሰራት ምድብ (ለ) ሕንፃ ብር 3,000.00 እና ምድብ (ሐ) ሕንፃ ብር 5,000.00 ይከፈላል።

፰. ያለማስታወቂያ ሥራ መጀመር ምድብ (ለ) ሕንፃ ብር 2,000.00 እና ምድብ (ሐ) ሕንፃ ብር 4,000.00 ይከፈላል።

፱. ያለፍቃድ የግንባታ ዕድሳት ማድረግ ምድብ (ሀ) ሕንፃ ብር 2,000.00፣ ምድብ (ለ) ሕንፃ ብር 3,000.00 እና ምድብ (ሐ) ሕንፃ ብር 5,000.00 ይከፈላል።

፲. ያለፍቃድ የማስፋፋት ሥራ ማከናወን ምድብ (ሀ) ሕንፃ ብር 2,000.00፣ምድብ (ለ) ሕንፃ ብር 3,000.00 እና ምድብ (ሐ) ሕንፃ ብር 5,000.00 ይከፈላል።

፲፩. ያለፍቃድ ግንባታ የማፍረስ ሥራ ማከናወን ምድብ (ሀ) ሕንፃ ብር 2,000.00፣ምድብ (ለ) ሕንፃ ብር 3,000.00 እና ምድብ (ሐ) ሕንፃ ብር 5,000.00 ይከፈላል።

፲፪. በግንባታ ወቅት መወሰድ የሚገባቸውን የጥንቃቄ እርምጃዎች አለመውሰድ ምድብ (ለ) ሕንፃ ብር 2,000.00 እና ምድብ (ሐ) ሕንፃ ብር 3,000.00 ይከፈላል።

፲፫. የሕንፃ መጠቀሚያ ፍቃድ ሳይገኝ መጠቀም ምድብ (ለ) ሕንፃ ብር 2,000.00 እና ምድብ (ሐ) ሕንፃ ብር 3,000.00 ይከፈላል።

፲፬. ከዚህ በላይ ያልተመለከቱ ጥፋቶች ተፈጽመው ሲገኙ እንደጥፋቱ ክብደት ለየሕንፃ ምድቡ ከተመለከቱት ቅጣቶች ውስጥ ተመጣጣኝ የሆነውን ቅጣት ይከፍላል።

፲፭. ከከተማ መሬት እና ከውጭ ማስተዋወቅ ጋር በተያያዘ ደንብ በመተላለፍ የሚጣል መቀጫ

በሠንጠረዥ አስራ አራት ተመልክቷል።

ሠንጠረዥ አስራ አራት፦ የከተማ መሬት እና የውጭ ማስተዋወቅ ሥራ ህግን በመተላለፍ ወይም ባለመጠበቅ የሚጣል መቀጫ የመጣኔ ማዕቀፍ

ተ ቁ	የጥፋት ዓይነቶች	መለኪያ	ፊርጅ አራት		ፊርጅ አምስት			
			መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳብ (ለፊርጅ አራት)	የውሳኔ ሃሳብ (ለፊርጅ አምስት)
1	በግል ይዞታ ላይ ያለፈቃድ ቤት መስራት ግንባታ ማካሄድ	ብር	1,000	1,750	1,000	1,500	1000	1000
2	ባልተፈቀደ ቦታ ላይ ቤት መስራት ግንባታ ማካሄድ	ብር	3,000	4,500	3,000	4,500	3000	3000
3	ያልተፈቀደ ቦታ ማጠር	ብር	800	1000	500	1000	800	500
4	ያልተፈቀደ ቦታ በማጠሩ ማስጠንቀቂያ ደርሶት ያላስተካከለ እና የመጀመሪያ ቅጣት ለመክፈል ፍቃደኛ ላልሆነ	ብር	400	500	400	500	400	400
5	ባልተፈቀደ ቦታ አሸዋ፥ ድንጋይ አፈርና እንጨት ማራገፍ እንዲሁም የግንባታ ፍርስራሽ እና ተራፊ የግንባታ ማቴሪያል ማከማቸት	ብር	80	115	80	115	100	100
6	ባልተፈቀደ ቦታ ለሰርግ፣ ለምርቃት ... ወዘተ ድንኳን ወይም ዳስ በመንገድ ዳር መጠቀም	ብር	300	400	200	300	300	200
7	የወሰን ድንጋይ መንቀል፣ጉዳት ማድረስ፣ ማናጋት	ብር	200	500	200	500	200	200

ተቁ	የጥፋት ዓይነቶች	መለኪያ	ፈርጅ አራት		ፈርጅ አምስት			
			መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	መነሻ መጣኔ	ከፍተኛ መጣኔ	የውሳኔ ሃሳብ (ለፈርጅ አራት)	የውሳኔ ሃሳብ (ለፈርጅ አምስት)
8	ባልተፈቀደ ቦታ ማስታወቂያ የሚለጥፍ ለአንድ ጊዜ	ብር	50.00	200.00	50.00	100.00	50	50
9	ባልተፈቀደ ቦታ የንግድ ወይም መለያ ምልክቶች መትከል ለመጀመሪያ ጊዜ	ብር	150.00	200.00	150.00	100.00	150	100
10	ባልተፈቀደ ቦታ የንግድ ወይም መለያ ምልክቶች መትከል ለሁለተኛ ጊዜ	ብር	300.00	400.00	300.00	400.00	300	300
11	ባልተፈቀደ ቦታ የንግድ ወይም መለያ ምልክቶች መትከል ለመጨረሻ ጊዜ	ብር	500.00	600.00	500.00	600.00	500	500
12	ሳይፈቀድ በጨርቅ፣ በሸራ ወይም በሌሎች ባነሮችን መዘርጋት	ብር	80.00	150.00	50.00	100.00	80	50

፳፱. ክፍያ ስለ ማስታወቅ

፩. የገቢዎች ጽ/ቤት ማንኛውም ሰው የሚፈለግበትን ዓመታዊ የከተማ መሬት ኪራይ እና የከተማ ቤት ግብር በአባሪ አንድ በተመለከተው የማስታወቂያ ቅጽ መሠረት በማዘጋጀት በሐምሌ ወር እንዲደርሰው ሊያደርግ ይችላል።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የሚዘጋጀው ማስታወቂያ የዘመኑና ውዝፍ ክፍያ፣ ወለድ እና ቅጣትን ማካተት አለበት።

፴. የከተማ ቤት ግብር፣ የከተማ መሬት ኪራይ እና የአገልግሎት ክፍያ የመክፈያ ጊዜያት

፩. የዘመኑ ዓመታዊ ክፍያ በበጀት ዓመቱ ውስጥ መከፈል አለበት።

፪. የአገልግሎት ክፍያዎች አገልግሎቱ እንደተሰጠ ተጠቃሚው መክፈል አለበት።

፫. የከተማ መሬት የሊዝ ክፍያ፣ በሊዝ ውል መሠረት የሚከፈል የሊዝ ቅድመ ክፍያ፣ዓመታዊ ክፍያ፣ቅጣትና ወለድ በሊዝ አዋጁና ደንብ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል።

፬. ለአገልግሎት የሚከፈለው የአገልግሎት ዋጋ በዚህ ሞዴል መመሪያ በተሰጠ ማዕቀፍ መካከል የሚወሰን የመጠኔ ተመን ይሆናል።

፭. የአገልግሎት ተጠቃሚ ማንኛውም ሰው የአገልግሎት ክፍያዎችን በተናጥልና አገልግሎቶቹ በተጠየቁ ጊዜ መክፈል አለበት።

፮. ለእያንዳንዱ የአገልግሎት ዓይነት የሚፈጸመው ክፍያ ለእያንዳንዱ አገልግሎት ለብቻ በገቢ አይነትና ዓርዕስት መከፈል አለበት።

፯. ከአገልግሎት ክፍያ ነፃ ተብለው የተመለከቱት አገልግሎቶች ወይም በሌላ ሕግ ከአገልግሎት ክፍያ ነፃ የተደረጉ አገልግሎቶች ከክፍያ ነጻ ናቸው።

፴፩. ክፍያ ስለመቀበል

፩. ክፍያ መቀበል ያለበት ገቢ እንዲሰበስብ ስልጣን የተሰጠው አካል ነው።

፪. በክልሉ ፋይናንስ ቢሮ በወጣው የደረሰኞች አያያዝና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 27/2010 አንቀጽ (13) ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ሁሉም ከተሞች ማዘጋጀ ቤታዊ የአገልግሎት ክፍያ ገቢ እንዲሰበሰቡ በህግ ስልጣን የተሰጣቸውና የተፈቀደላቸው መሥሪያ ቤቶች ገቢውን ለመሰብሰብ የሚያገለግል የገቢ ደረሰኝ

መ/ሂ/7/ሐ የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ኃላፊ በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ለተወከለው ባለሙያ ከፋይናንስ መምሪያ ወይም ጽ/ቤት ሲፈቀድ በሞዴል 22 ወጪ በማድረግ የማዘጋጃ ቤታዊ ክፍያን ይቀበላል።

፫. በፋይናንስ ቢሮ አማካኝነት በሚታተም ደረሰኝ መ/ሂ/7/ሐ ካልሆነ በስተቀር በማናቸውም ምክንያት በሌላ የደረሰኝ ህትመት ክፍያ መቀበል አይቻልም፤ ሆኖም የቴክኖሎጂ መዘመንን ታሳቢ በማድረግ በኤሌትሮኒክስ ደረሰኝ ክፍያ መቀበል ይቻላል።

፬. ክፍያ እንዲቀበል የተመደበ ሠራተኛ ለተቀበለው ክፍያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተገለጸው ደረሰኝ ተገቢ የሆኑ መረጃዎችን በመሙላት ደረሰኝ በመቁረጥ ለከፋይ መስጠት አለበት።

፴፪. ገቢ ስለማድረግ

፩. ገቢን ለመሰብሰብ የተመደበው ሰው የሰበሰበውን ወይም የተቀበለውን ወይም የተፈፀመለትን

ክፍያ በየቀኑ የሥራ ሰዓት ማብቂያ ወይም እጅግ ቢዘገይ በሚቀጥለው የሥራ ቀን ጠዋት

አግባብ ባለው የባንክ ሂሳብ ውስጥ ገቢ ማድረግ አለበት::

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአካባቢው የባንክ አገልግሎት በማይኖርበት ወቅት በመ/ሂ 65 በመዘርዘር እና መ/ሂ 64 በመረከብ በፋይናንስ ጽ/ቤት ካዝና ገቢ እንዲሆን ይደረጋል።

፫. በአንቀጽ (፴፫) ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሠረት የተደራጀው መረጃ በፋይናንስ በ IBEX በገቢ ዓርዕስት እንዲመዘገብ በየቀኑ ወይም በሳምንት ክፍያ የተቀበለ ሠራተኛ ለፋይናንስ በማቅረብ እንዲመዘገብ ማድረግ እና የፋይናንስ ባለሙያ የቀረበለትን መረጃ መሠረት በማድረግ ምዝገባ ማካሄድ አለበት።

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የፋይናንስ ቢሮ በየወሩ በገቢ

ርዕስና ኮድ የተመዘገበውን የገቢ መረጃ ለገቢዎች ቢሮ ፕሪንት እየተደረገ በሸኚ ደብዳቤ

እንዲተላለፍ ያደርጋል፣ የገቢዎች ቢሮም በየወሩ በመከታተል የገቢዎች እና የፋይናንስ የገቢ

መረጃ ወጥና የተናበበ መሆኑን ያረጋግጣል ።

፴፫. ክፍያ የመቀበል እና ገቢ የማድረግ ኃላፊነትና ተጠያቂነት

፩. ክፍያ የተቀበለ ሠራተኛ በደረሰኝ ላይ ትክክለኛና ተገቢ የሆነውን የገቢ ዓርዕስት እና የተከፈለበትን ምክንያት በመመዝገብ መረጃውን በየጊዜው በማጠናከር ለቅርብ ኃላፊው ማቅረብ አለበት።

፪. በገቢዎች ጽ/ቤት የደንበኞች አገልግሎት፣ታክስ አወሳሰንና አሰባሰብ ዳይሬክቶሬት

የገቢ አሰባሰብ እና የደረሰኝ አጠቃቀም ላይ ክትትል ያደርጋሉ።

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በአፈፃጸም ላይ የሚስተዋለውን ክፍተት ለመቀነስ በገቢዎች ጽ/ቤት የደንበኞች አገልግሎት፣የደንበኞች አገልግሎት ታክስ አወሳሰንና አሰባሰብ ዳይሬክቶሬት ክፍያ የመቀበል እና የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት በማንዋል የተደገፈ የማድረግ፣ክፍያ ለሚቀበል ሠራተኛ በቂ ግንዛቤ የመፍጠር እና በተዘረጋው የአሰራር ስርዓት ተፈፃሚ ስለ መሆኑ ክትትል ያደርጋል።

፬.በዞን ገቢዎች መመሪያ የታክስ ሕግ ማስከበር ዳይሬክቶሬት የማህደር ምርመራ እና ስጋትን መሠረት ያደረገ ክትትል በማድረግ የህግ ማስከበር ተግባር ያከናወናል።

፭. በውስጥ እና በውጭ ኦዲት የደረሰኝ አጠቃቀም፣ የገቢ አሰባሰብ፣ የገቢ ርዕስ ምዝገባ...ወዘተ በተፈቀደው ህግ መሠረት ተፈፃሚ ስለ መሆኑ ይረጋገጣል።

፮. በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት መስሪያ ቤቶች የደረሰኞችና የሌሎች የህትመት፣ አያያዝና አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 27/2010 ክፍል ሰባት ጥፋትና ቅጣት በተደነገገው በአንቀጽ (25) ቀላል ጥፋትና ቅጣት እና በአንቀጽ (26) የጠፋ ጥራዝ ወይም ቅጠል የሚያስከትለው ከባድ ቅጣት በተደነገገው መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል።

፯. በግዴለሽነት ወይም ሆን ብለው ህገ-ወጥ ተግባር በሚፈጽሙ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ላይ በገቢዎች ጽ/ቤት የአሠራርና የሠራተኞች አስተዳደር ደንብ ቁጥር 94/2004 እና በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት የባለስልጣኑ የሠራተኞች ሥነ-ምግባር መመሪያ ቁጥር 15/2004 መሠረት ተጠያቂ ይሆናሉ።

፴፱.ዓመታዊ ክፍያን በማዘግየት የሚጣል መቀጫና ወለድ

፩. ዓመታዊ ክፍያ በዘገየበት የሚጣለው መቀጫ በየወሩ 2% ቅጣት ይከፈላል።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚጣለው መቀጫ መከፈል ካለበት ክፍያ መጠን 50% መብለጥ የለበትም።

፫. በዘገየበት የሚጣለው ወለድ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማበደሪያ ከፍተኛ ተመን መሠረት ይከፈላል። የወለድ መጣኔው የባንክ የማበደሪያ ተመን ሲለወጥ አብሮ ይለወጣል።

፱. የመቀጫው መታሰብ መጀመር ገቢ ለመሰብሰብ የተፈቀደለት አካል ሌሎች ህጋዊ እርምጃዎችን ከመውሰድ የሚያግደው አይሆንም።

፮. ከቅጣትና ወለድ የሚሰበሰብ ገንዘብ ደንብና መመሪያን በመተላለፍ ቅጣት (1746) በሚል የገቢ ርዕስ ምዝገባ ይካሄዳል።

፯. በአንቀጽ (፭፱) ንዑስ አንቀጽ (፮) በደረሳቸው ማስታወቂያ የጊዜ ገደብ ውስጥ መጥተው የማይከፍሉ የከተማ መሬት ኪራይ እና የከተማ ቤት ግብር ባለዕዳዎች የይዞታ ማረጋገጫ ላልተወሰነ ጊዜ በመሬት ልማትና ማኔጅመንት እንዲታገድ ይደረጋል።

፯. የሊዝ ዓመታዊ ክፍያ በውሉ መሠረት በማይከፈል ላይ በዘገየበት የሚጣል መቀጫና ወለድ በሊዝ አዋጅ 721/2004 አንቀጽ (20) ንዑስ አንቀጽ (5) በተደነገገው መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል።

፰. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) በተሰጠው የጊዜ ገደብ ክፍያውን ያልፈፀመ ማንኛውም ሰው በሕግ ይጠየቃል።

፬፭. ስለ ቅሬታ አቀራረብ

፭. በአንቀጽ (፭፱) ንዑስ አንቀጽ (፭) በተሰጠው ማስታወቂያ ላይ ቅር የተሰኘ ባለይዞታ በገቢዎች ቢሮ በአገልግሎት ቅሬታ ማስተናገጃ መመሪያ ቁጥር 34/2011 አንቀጽ 12 በተሰጠው የጊዜ ገደብና የቅሬታ ማቅረቢያ ደረጃዎች መሠረት ቅሬታ ማቅረብ ይችላል::

፪. የቅሬታ ማጣራት እና የውሳኔ አሰጣጥ በአገልግሎት ቅሬታ ማስተናገጃ መመሪያ ቁጥር 34/2011 የተከተለ ይሆናል።

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) መሠረት የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የቅሬታው ምንጭ ከአገልጋይ ሥነ-ምግባር ጋር የተያያዘ ከሆነ አቤቱታውን ለወረዳው ወይም ለልዩ ወረዳ አስተዳደር ወይም የከተማው ከንቲባ ወይም ወረዳው ወይም ልዩ ወረዳ ወይም ከተማው ለሚሰይመው አካል ሊያቀርብ ይችላል።

፬. በገቢ አሰባሰብ ከክፍያ አንፃር፣በስሌት፣በስም ዝውውር ገበያ ዋጋ የሕንፃ ግመት እና በሌሎች የታክስ ይዘት ያላቸው ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው በገቢዎች ጽ/ቤት “የታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ለማቋቋምና የአሰራር ሥርዓቱን ለመወሰን የወጣ መመሪያ

ቁጥር 33/2011" መሠረት ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል። የቅሬታ ማጣራት እና የውሳኔ አሰጣጥ በመመሪያው መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል።

፴፯. በከተማው አስተዳደር ወይም ወረዳ ወይም ልዩ ወረዳ መመሪያ በሚዘጋጅበት ወቅት

፩. ከተማው በተመደበበት ፈርጅ መሠረት የመጣኔ ተመን በሚወሰንበት ወቅት በየገቢ ርዕሱ ከሰንጠረዥ አንድ እስከ አስራ አራት የተመለከተውን የዝቅተኛና የከፍተኛው መጣኔ ተመን ማዕቀፍ የጠበቀ ይሆናል።

፪. አንድ ከተማ በማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ከተመደበበት ፈርጅ የላቀ ወይም ያነሰ ሆኖ ሲገኝ በቂ ማስረጃና ማብራሪያ በማቅረብ ከተመደበለት ማዕቀፍ ወደ ላይ ወይም ወደታች የተመለከተውን የመጣኔ ማዕቀፍ አስፈቅዶ ሊጠቀም ይችላል።

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው አግባብ የተዘጋጀው ረቂቅ መመሪያ ላይ የከተማ ነዋሪ ህብረተሰብ ተሳትፎ ለማረጋገጥ እና የሚሰጡ አስተያየቶችን ለማካተት እንዲቻል በከተማው ወይም ወረዳ ወይም ልዩ ወረዳ ምክር ቤት ከመጽደቁ በፊት በቋሚ ኮሚቴ አባላት አማካኝነት ከከተማ ነዋሪ ጋር ውይይት ይደረጋል።

፬. በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፴፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) ለዞን የተሰጠው ሃላፊነትና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ለሚቀርብ ጥያቄ እና አዳዲስ የገቢ አይነት ለማካተት ሲያስፈልግ ለክልሉ ገቢዎች በማቅረብ ስምምነት እና ፍቃድ ማግኘት ያስፈልጋል።

ክፍል ሦስት

ኃላፊነትና ተግባር

፴፰. የወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ኃላፊነትና ተግባር፣

፩. በዚህ መመሪያ ለከተማው ፈርጅ በተሰጠው ማዕቀፍ መሠረት የመጣኔ ተመን በመለየት አስተያየት እንዲሰጥበት ለዞን ያስተላልፋል።

፪. በዞኑ አስተያየት ከተሰጠበት በኃላ በወረዳው ምክር ቤት ያስወስናል፤ ሲፈቀድም ገቢ ይሰበስባል።

፮.በወረዳው ምክር ቤት ከመጽደቁ በፊት በቋሚ ኮሚቴ አባላት አማካኝነት የከተማው ነዋሪዎች ውይይት እንዲያደርጉበት የተዘጋጀውን ረቂቅ መመሪያ ያቀርባል።

፯.በወረዳው ምክር ቤት የጸደቀውን መመሪያ ለዞን እንዲሁም ለወረዳ፣አስፈጻሚ አካላት እና ባለድርሻ አካላት እንዲደርስ ያደርጋል።

፰. ከአገልግሎት ክፍያ የተሰበሰበውን የገቢ መረጃ ይይዛል፣ ያደራጃል፣ ያሰራጫል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል።

፱. የአገልግሎት ክፍያ ለመሰብሰብ የሚያስችል ምቹ እና ቀላል ሁኔታዎችን ለማንኛውም ሰው አመቺና ተደራሽ ያደርጋል።

፲፩. የከተማ ማዘጋጃ ቤት ኃላፊነትና ተግባር፣

፩. በተሰጠው አገልግሎት መጠን ሊከፈል የሚገባውን የአገልግሎት ክፍያ መጠን በመለየት ክፍያ ለሚቀበል ያስተላልፋል።

፪. ዓመታዊ ኪራይ፣ ግብር እና የአገልግሎት ክፍያ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መሠረታዊ የሆኑ መረጃዎችን ወቅታዊ በማድረግ ይይዛል፣ ያደራጃል፣ ለገቢዎች ጽ/ቤት እና ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል።

፫. የአገልግሎት ክፍያ፣ዓመታዊ ኪራይና ግብር በወቅቱ ስለ መፈጸማቸውን ክትትል በማድረግ የገቢ መረጃ ይይዛል።

፬. ሕግን በመተላለፍ ወይም ባለመጠበቅ የሚጣል መቀጫን ይጥላል፣ ክፍያ ለሚቀበሉ ያስተላልፋል፣ የተወሰነባቸውን ቅጣት ስለመክፈላቸው ክትትል ያደርጋል። ክፍያ ባልፈጸሙት ላይ ተከታታይነት ያለው እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል።

፲፪. የአገልግሎት ክፍያ ፈጻሚ ሰው ኃላፊነትና ተግባር፣

፩. አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት ወይም ማህበር ክፍያ የፈፀመበትን ደረሰኝ በአግባቡ የማስቀመጥ እና እንዲያሳይ ወይም እንዲያቀርብ በተጠየቀ ጊዜ ማቅረብ አለበት።

፪. የይዞታ ወይም የንብረት ባለቤትነት ህጋዊ ውል ወይም ሌሎች የባለቤትነት ወይም ንብረት

ለመጠቀም ማረጋገጫነት የሚገልጹ ማስረጃዎች እንዲያቀርብ ሲጠየቅ ማቅረብ አለበት።

፫. አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት ወይም ማህበር ለሚሰጠው አገልግሎት ክፍያ መፈጸም አለበት።

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፴፭. ስለተጠያቂነት

ይህን መመሪያ በማንኛውም መልኩ በሚጻረር ተግባር ውስጥ በመሳተፍ ያለአግባብ የፈጸመ፣ ያስፈጸመ እንዲሁም የተባበረ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባላቸው የሀገሪቱና የክልሉ ህጎች በተደነገገው መሰረት ተጠያቂ ይሆናል።

፴፮. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት።

፴፯.ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

፴፰. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

የገቢዎች ጽ/ቤት ሞዴል መመሪያውን መነሻ በማድረግ መመሪያ የማውጣት ስልጣን ይኖራቸዋል።

፴፱. መመሪያን ስለመፈፀም

የወረዳው የገቢዎች ጽ/ቤት እና ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ይህንን መመሪያ የመፈፀም እና የማስፈፀም ስልጣን አላቸው።

፵. መመሪያ ስለማሻሻል

ይህን መመሪያ ማሻሻል ባስፈለገ ጊዜ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ እና በገቢዎች ጽ/ቤት እየተጠና መሻሻል ይችላል።

፵፩. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሐምሌ 1 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

የወረዳው አስተዳዳሪ ፊርማ

<u>የወረዳው አስተዳዳሪ ስም</u>

የጌታ ወረዳ አስተዳደር

<u>ቋንጤ</u>

<u>የከተማው አስተዳደር ምክር ቤት ክብ ማህተም በእያንዳንዱ ገፅ ላይ ይደረግ /ከፀደቀ በኋላ/</u>

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት በጉራጌ ዞን የጌታ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት የከተማ መሬት ኪራይ እና የከተማ ቤት ግብር ማስታወቂያ ቅጽ

ቁጥር _

ቀን ___

የመዝገብ ቁጥር _____

የባለይዞታው የፕሎት መለያ ቁጥር _____

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ____

የባለቤት ሙሉ ስም _____

አድራሻ በደቡብ ክልል በ_____---------- ዞን በ---------- ወረዳ በቤት ቁጥር_____

- የ.....ዓ.ም የመሬት ኪራይ ብር _____የቤት ግብር ብር_____
- የ.....ዓ.ም የመሬት ኪራይ ብር _____የቤት ግብር ብር_____
- የ.....ዓ.ም የመሬት ኪራይ ብር _____የቤት ግብር ብር_____

የከተማ መሬት እና ቤት ጋር ተያያዥነት ያላቸው የአገልግሎት ክፍያዎች ተመን ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር..... /2014 አንቀጽ 29 መሠረት ብር_____በፊደል_____ብር ያለብዎት በመሆኑ ይህ ማስታወቂያ በደረሰዎ በሰላሳ/30/ ቀናት ውስጥ እንዲከፍሉ እናስታውቃለን።

የከተማ መሬት ኪራይ እና የከተማ ቤት ግብር ማጠቃለያ

የበጀት ዓመቱ የከተማ መሬት ኪራይ እና የከተማ ቤት ግብር _____፣

ውዝፍ ያልተከፈለ ብር_____መቀጫ ብር_____ወለድ ብር___

ጠቅላላ የተወሰነ ክፍያ፣ መቀጫና ወለድ_____

የጽ/ቤት ኃላፊ ስም _____

ፊርማ _____

ቀን _____ማስታወቂያው፡-

ለባለይዞታው የተሰጠበት ቀን _____

የተቀበለው ሰው ስም _____ የኃላፊነት ደረጃ_____ ፊርማ _____ ቀን _____

የሰጠው ሠራተኛ ስም _____ ፊርማ _____ ቀን _____